# የዓለም ሥራ ድርጅት

## በሥራው ዓለም ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በተመለከተ የወጣ የተግባር መመሪያ

**ጄኔቫ 2001**

የዓለም ሥራ ድርጅት ጽሕፈት ቤት፣ ጄኔቫ

# ማውጫ


መቅድም ....... 1
1. ዓላማ ....... 2
2. አጠቃቀም ....... 2
3. የመመሪያው የሽፋንና በውስጡ የተካተቱ ቃላት ....... 2
3.1. ሽፋን ....... 2
3.2. በመመሪያው ውስጥ የሚያገለግሉ ቃላት ....... 3
4. ቁልፍ መርሆዎች ....... 5
4.1. ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የሥራ ቦታ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ/ማወቅ ....... 5
4.2. መድልዎ አልባነት ....... 5
4.3. የፆታ እኩልነት ....... 5
4.4. ጤናማ የሥራ አካባቢ ....... 5
4.5. ማኅበራዊ ውይይት ....... 6
4.6. ከቅጥርና ከሥራ ሂደቶች ለማግለል ሲባል የሚደረግ ምርመራ ....... 6
4.7. ምሥጢራዊነት ....... 6
4.8. የቅጥር ግኙኙነት ቀጣይነት ....... 6
4.9. መከላከል ....... 6
4.10. እንክብካቤና ድጋፍ ....... 7
5. ጠቅላላ መብቶችና ኀላፊነቶች ....... 7
5.1. መንግሥታትና ኀላፊነት የተሰጣቸው ባለሥልጣኖቻቸው ....... 7
5.2. አሠሪዎችና ማኅበሮቻቸው ....... 10
5.3. ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ....... 12
6. በመረጃና በትምህርት የሚደረግ መከላከል ....... 14
6.1. መረጃና ግንዛቤን ከፍ ማድረግ ዘመቻዎች ....... 14
6.2. ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ....... 15
6.3. በፆታ ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች ....... 16
6.4. ከጤና ማሳደግ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣም ....... 17
6.5. የጠባይ ለውጥን ለመደገፍ የሚወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች ....... 17
6.6 ማኅበረሰብን የማስተማር ፕሮግራሞች ....... 17
7. ሥልጠና ....... 18
7.1. ለሥራ አስኪያጆች፣ ተቆጣጣሪዎችና ለአስተዳደር ኃላፊዎች የሚሰጥ ሥልጠና ....... 18
7.2. ለአቻ አስተማሪዎች (peer educators) የሚሰጥ ሥልጠና ....... 19
7.3. ለሠራተኞች ተወካዮች የሚሰጥ ሥልጠና ....... 19
7.4. ለጤናና ለደህንነት ኃላፊዎች የሚሰጥ ሥልጠና ....... 20
7.5. ለማምረቻ/ለሥራ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች የሚሰጥ ሥልጠና ....... 20
7.6. ከሰው ደምና ከሌሎች የሰውነት ፈሳሶች ጋር ለሚነካኩ ሠራተኞች የሚሰጥ ሥልጠና ....... 21
8. ምርመራ ....... 21
8.1. በምልመላና በቅጥር የሚደረግ ክልከላ ....... 21
8.2. ለመድህን ዋስትና ዓላማዎች የሚደረግ ክልከላ ....... 22
8.3. የበሽታ ክትትል ጠቅላላ ጥናት ....... 22
8.4. በፈቃደኛነት መመርመር ....... 22
8.5. በሥራ ምክንያት ከሚደርስ መጋለጥ በኋላ የሚደረጉ ምርመራዎችና ህክምና ....... 23
9. እንክብካቤና ድጋፍ ....... 23
9.1. ከሌሎች ከባድ ህመሞች ጋር ያለው አቻነት ....... 23
9.2. የምክር አገልግሎት ....... 24
9.3. የሙያና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች ....... 25
9.4. ከራስ አገዝና በማኅበረሰብ ላይ ከተመሠረቱ ቡድኖች ጋር የሚኖሩ ግንኙነቶች ....... 25
9.5. ጥቅሞች ....... 25
9.6. የማኅበራዊ ዋስትና ሽፋን ....... 26
9.7. ግለኝነትና ምሥጢራዊነት ....... 26
9.8. የሠራተኛና ቤተሰብ እርዳታ ፕሮግራሞች ....... 26
አባሪ 1 ....... 28
ስለ ወረርሽኙና ውጤቶቹ መሠረታዊ ጭብጦች ....... 28
ስለ ኤች.አይ.ቪ. እና ኤይድስ ጭብጦች ....... 28

**በሥነ ሕዝብና በሠራተኛ ኃይል ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ..................29**
**ለተጎጂነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች..................30**
**አጠቃላይ ጭብጦች..................30**
**በአንዳንድ ሠራተኞች ዘንድ የበሽታውን አደጋ የሚያሳድጉ ጭብጦች ..................30**
**መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ያሉ ልዩ ፍላጎቶች..................32**
**የፆታ ገፅታ ..................32**
አባሪ 2..................35
**በሥራ ቦታ የሚደረግ የበሽታ ቁጥጥር..................35**
**ሀ. ጠቅላላ የደምና የሰውነት ፈሳሽ ጥንቃቄዎች..................35**
**ለ. ምርጥ መመሪያዎች በመከላከያ ቁጥጥር ላይ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች..................36**
አባሪ 3..................37
**በሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲ ስለ ማቀድና ተግባራዊ የማድረግ መከታተያ ዝርዝር (ማመሳከሪያ)..................37**

# መቅድም

የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ወረርሽኝ ባሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ ቀውስ ከመሆኑ በላይ በልማትና በማኅበራዊ እድገት ላይ የተደቀነ ከባድ ፈተና ነው፡፡ በብዛት በተጠቁት አገሮች ወረርሽኙ በአሥርተ ዓመታት የተገኙትን የልማት ዕሤቶች እየሸረሸረ፣ ኤኮኖሚን እያዳከመ፣ ደህንነትን እያናጋና የኅበረተሰብን መረጋጋት እያናወጠ ይገኛል፡፡ ይህ ወረርሽኝ አስቀድሞ ፍጹም ጎጂ የሆነ ተጽእኖ ባሳደረባቸው ከሳሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች ቀውሱ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ እንዲፈጠር አስገድዷል፡፡

በግለሰቦችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ከሚያሳድረው ሥቃይ በላይ ወረርሽኙ የኅበረተሰቦችን ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮችን በጥልቅ በመጉዳት ላይ ይገኛል፡፡ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በሥራ ዓለም ላይ የተደቀነ ዋነኛ አደጋ ከመሆኑ በላይ በጣም አምራች ክፍል የሆነውን የሠራተኛ ኃይል ከመጉዳትና ገቢውንም ከማቆርቆዙም በላይ በተለያዩ ዘርፎች በተሰማሩት ኢንተርፕራይዞችም ላይ በምርት መቀነስ፣ በሠራተኛ ወጪ መጨመርና ልምድና ሙያ ያላቸው ሠራተኞች መታጣት ምክንያት ከፍተኛ ወጪ እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በተለይ የህመሙ ተጠቂ በሆኑ የቫይረሱ ተሸካሚ ሠራተኞችና ሰዎች ላይ ከሚደረገው መድልዎና ከሚነጣጠረው ጐጂ የሆነ አመለካከት (stigmatization) የተነሣ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የሥራ ቦታን መሠረታዊ መብቶች የሚነካ ሆኖአል፡፡ የወረርሽኙ ተጽእኖ ሴቶችንና ሕፃናትን ጨምሮ በቀላሉ ተጐጂ በሆኑት የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደርስ ከመሆኑም በላይ ሕፃናትን ያለ ዕድሜያቸው በሥራ የማሰማራት ችግርን (child labour) ያባብሳል፡፡

ስለዚህ ነው የዓለም ሥራ ድርጅት ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በተመለከተ ጠንካራ መግለጫና የተግባር መመሪያ ለማውጣት ቆርጦ የተነሣው፡፡ መመሪያው ወረርሽኙ እንዳይስፋፋ፣ በሠራተኞችና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚደርሰውን ተጽእኖ ለመቀነስ፣ እንዲሁም በሽታውን ለመቋቋምና ማኅበራዊ መከላከልን ለማጐልበት ዓይተኛ መመሪያ ይሆናል፡፡ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የሥራ ቦታ ችግር መሆኑን እውቅና መስጠትን፣ የሥራ ቅጥር መድልዎን ማስወገድና የፆታ እኩልነትን፣ ምርመራና ምሥጢርነቱን (screening and confidentiality)፣ ማኅበራዊ ውይይትን፣ መከላከልን፣ እንክብካቤንና ድጋፍን በተመለከተ ወረርሽኙን በሥራ ቦታ ላይ ለመቋቋም የሚያስችል መሠረታዊ መርሆ ይሆናል፡፡

ይህ መመሪያ በዓለም ሥራ ድርጅትና ሦስት አካላዊ አባሎቹ (Tripartite Constituents)፣ እንዲሁም የዓለም አቀፍ አጋሮቹ መካከል የተደረገ ትብብር ውጤት ነው፡፡ የተግባር መመሪያው ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለአሠሪዎችና ለሠራተኛ ማኅበራት፣ እንዲሁም ለሌሎች ማኅበራዊ አጋሮች ተገቢ የሥራ ቦታ ፖሊሲ ለማርቀቅ፣ የመከላከልና የእንክብካቤ ፕሮግራሞችን ለማውጣት፣ እንዲሁም መደበኛ ባልሆነው የኤኮኖሚ ዘርፍ (informal sector) ውስጥ ለሚገኙ ሠራተኞች ትኩረት መስጠት ይቻል ዘንድ ስልት ለማውጣት ከፍተኛ ተግባራዊ መመሪያ ይሆናል፡፡ ይህ የዓለም ሥራ ድርጅት የተግባር መመሪያ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በዓለም አቀፍ ደረጃ በመከላከል ረገድ ለሚካሄደው ጥረት ታላቅ አስተዋጽኦ ይሆናል፡፡

በሚደርሰው ማኅበራዊና ሰብአዊ ቀውስ አንጻር መመሪያው የተረጋጋ የሥራ ሂደትን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ ቀደም ሲል ይህን ቀውስ ለመቋቋም በተደረገው ሙከራ ጠቃሚ ትምህርት ተገኝቷል፡፡ ጥቂት አገሮች የህመሙን መስፋፋት በመቀነስና ውጤቱ በግለሰቦችና በማኅበረሰባቸው ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ በማለዘብ ረገድ ስኬታማ ደረጃን ተጐናጽፈዋል፡፡ በጣም ጥሩ የሆኑት ልምዶች ሀቀኛ አመራርን፣ ዘርፈ-ብዙ አቀራረብን፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎችን ጨምሮ ከኅብረተሰቡ ጋር አጋርነትንና ትምህርትን ያጠቃልላሉ፡፡ እነዚህ መሠረተ ሃሳቦች በመርሆዎችና ለውጤታማነቱ በማኅበራዊ አጋሮች ተሳትፎ ሚና ውስጥ የተንጸባረቁ ናቸው፡፡

ይህ መመሪያ አሁን ባሉት ችግሮች ላይ የሚያተኩር ከመሆኑ በላይ ወደፊት ወረርሽኙ በሥራው ዓለም የሚያሳድረውን ተጽእኖ የሚተነብይ ሰነድ ነው፡፡ የዓለም ሥራ ድርጅት በዚህ መመሪያ አማካይነት ከኤች.አይቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞችና ሰዎችን መብትና ክብር ለመጠበቅ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ድጋፎቹን ያሳድጋል፡፡

ጄኔቫ፣ ሰኔ 2001

ሁዋን ሶማቪያ
ዋና ዳይሬክተር

# 1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሥራው ዓለም የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ወረርሽኝን በተመለከተ በአመርቂ ሥራ (Decent Work) አንጻር መሠረታዊ መርሆዎችን ለመዘርጋት ነው፡፡ መመሪያውም የሚከተሉትን ቁልፍ የተግባር መስኮች ይሸፍናል፡-

ሀ. ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መከላከል፤

ለ. ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በሥራው ዓለም ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ መቆጣጠርና መከታተል፤

ሐ. በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ለታመሙና ለተጠቁ ሠራተኞች የሚደረግ እንክብካቤና እገዛ፤

መ. በእርግጠኛ ወይም በሚገመት የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ አንፃር የሚፈጠረውን አሉታዊ አመለካከትና መድልዎ ማስወገድ፡፡

# 2. አጠቃቀም

ይህ መመሪያ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት መዋል አለበት፡-

ሀ. በድርጅቶች፣ በማኅበረሰብ፣ በአካባቢ፣ በዘርፍ፣ በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ተጨባጭ ተሳትፎዎችንና ምላሾችን ለማዳበር፤

ለ. በመንግሥታት፣ በአሠሪዎች፣ በሠራኞችና በተወካዮቻቸው፣ እንዲሁም በጤና ባለሙያዎች፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጉዳይ ልዩ ልምድ ባላቸውና ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካሎች (ይህ ማኅበረሰባዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሊጨምር ይችላል) መካከል የውይይት ሂደቶችን፣ ምክክሮችንና ሁሉ-አቀፍ ትብብሮችን ለማሳደግ፤

መ. ቀጥሎ በተዘረዘሩት አንጻር ከማኅበራዊ አጋሮች ጋር በመመካር መርሆዎቹ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ይኸውም፡-

- በብሔራዊ ሕጎች፣ በፖሊሲዎችና በፕሮግራሞች፤
- በሥራ ቦታ/በድርጅት ስምምነቶች፣ እና
- በሥራ ቦታ ፖሊሲዎችና በተግባር እቅዶች፡፡

# 3. የመመሪያው የሽፋንና በውስጡ የተካተቱ ቃላት

## 3.1. ሽፋን

ይህ መመሪያ፡-

ሀ. በመንግሥታዊ፣በሕዝባዊና በግሉ ዘርፍ የተሰማሩትን አሠሪዎችና ሠራተኞችን ሁሉ (ለሥራ ቅጥር የሚያመለክቱትን ጨምሮ)፣እና

ለ. መደበኛና መደበኛ ያልሆኑትን የሥራ ዘርፎች ይመለከታል::

## 3.2. በመመሪያው ውስጥ የሚያገለግሉ ቃላት

**ኤች.አይ.ቪ፤** (Human Immunodeficiency Virus (HIV)—ህዩማን ኢምዩኖዲፊሽንሲ ቫይረስ) በሰውነት ውስጥ በሽታን የመቋቋም ኃይልን በማዳከም ሙሉ በሙሉ ኤይድስ እንዲፈጠር የሚያደርግ ህዋስ (ቫይረስ) ነው::

**የተጠቁ ሰዎች፤** በኤች.አይ.ቪና ወረርሽኙ በሚያደርሰው ተጽእኖ ምክንያት ሕይወታቸው የተለወጠ ሰዎች::

**ኤይድስ፤** በእንግሊዝኛው Acquired Immune Deficiency Syndrome (AIDS)—አኳየርድ ኢምዩን ዲፊሽንሲ ሲንድሮም የሚባለው ምኅፃረ ቃል ሲሆን ካንሰርና ተያያዥ በሽታዎችን የሚመለከት ሲሆን እስከ ዛሬ ፈውስ እንዳልተገኘለት የሚጠቀስ የህክምና ሁኔታዎች ስብስብ ነው::

**መድልዎ፤** በዚህ መመሪያ ውስጥ ይህ ቃል ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በማካተት በሥራ ሥምሪትና በሙያ ላይ የሚደረገውን መድልዎ በሚመለከት የዓለም ሥራ ድርጅት በ1958 ዓ.ም. ባወጣው ድንጋጌ (ቁ. 111) በተሰጠው አገላለጽ መሠረት የሚካተት ይሆናል:: ሠራተኞችን በመሚመለከት በተገመተ የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ፣ እንዲሁም በፆታዊ ባሕርይ ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ መድልዎን ያካትታል::

**የአካል ጉዳተኛ ሰዎች፤** በዚህ መመሪያ ውስጥ ይህ ቃል በ1983 ዓ.ም. የአካል ጉዳተኞች ሙያዊ ተሀድሶና የሥራ ሥምሪት በሚመለከት በጸደቀው የዓለም ሥራ ድርጅት ድንጋጌ (ቁ. 159) መሠረት ይሆናል:: ይህም ማለት በሚታይ የአካልና የአእምሮ ጉዳት የተነሣ ተስማሚ የሥራ ሥምሪት ማግኘት፣ በዘላቂነት እየሠሩ የመቆየትና የማደግ እድሉ በጣም ዝቅ ያለበት ግለሰብ ማለት ነው::

**አሠሪ፤** በአንድ ብሐራዊ ሕግና ልምድ መሠረት በሁለቱ ወገኖች (በአሠሪውና በሠራተኞች) መካከል መብቶችና ግዴታዎችን በሚጠብቅ መልኩ ሠራተኞችን በጽሁፍ ወይም በቃል ስምምነት የሚቀጥር:: መንግሥታዊ፣ ሕዝባዊ ባለሥልጣኖች፣ የግል ድርጅቶችና ግለሰቦች አሠሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ::

**የጤንነትና ደህንነት አገልግሎት፤** በዚህ መመሪያ ውስጥ ይህ ቃል በ1985ቱ የመደበኛ ጤና አገልግሎቶች የዓለም ሥራ ድርጅት ድንጋጌ (ቁ. 161) እንደ ተገለጸው ያገለግላል:: ይኸውም በዋነኛነት የመከላከል ተግባር ሆኖ ከሥራ ጋር በተዛመደ መልኩ የበለጠ የአካልና የአእምሮ ጤናማነት እንዲኖር ለአሠሪዎች፣ ለሠራተኞቻቸውና ለተወካዮቻቸው ለማመቻቸት አስተማማኝና ጤናማ የሥራ አካባቢና የአሠራር ዘርፎች የመፍጠር አስፈላጊነትና አጠባበቁን የሚያማክር አገልግሎት ነው:: እንዲሁም የጤንነትና ደህንነት አገልግሎት እንደ ሠራተኞቹ የአካልና የአእምሮ ጤናማነትና ችሎታ መጠን ሥራን መቀበል እንዲችሉ ምክርን ይሰጣል::

**ተገቢ መመቻቸት፤** ከኤች.አይ.ቪ. ወይም ከኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች በሥራ ወይም በሥራ ቦታ በተግባራዊ መልኩ እንዲሳተፉ ወይም እንዲያድጉ ለማስቻል የሚደረግ ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ::

**ምርመራ፤** በቀጥታ (የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ) ወይም በተዘዋዋሪ (ጉዳት ላይ የሚጥል ጠባይ ክትትል)፤ ወይም አስቀድሞ ስለ ተደረጉ ምርመራዎችና ስለ ተወሰዱ መድኃኒቶች ጥያቄዎችን ማቅረብ::

**ተፈጥሮአዊ ፆታና ማኅበራዊ ፆታ፤**(sex and gender) በወንዶችና በሴቶች መካከል ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ልዩነቶች አሉ:: ፆታ የሚለው ቃል በተፈጥሮ የተወሰነውን የአካል ልዩነት ሲያመለክት፣ ማኅበራዊ የሚለው ቃል በማኅበራዊ ሚናዎች ውስጥ በወንዶችና በሴቶች መካከል ባለው ግንኙነት የሚታየውን ልዩነት ያመለክታል:: ተግባራዊ ሚናዎች በማኅበራዊ ተሳትፎ የሚታወቁ ሲሆን እንደየባህሉ በእድሜ፣ በመደብ፣ በዘርና በሃይማኖት፤ በመልክአ ምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በሰፊው ይለያያሉ::

**በግብረ ሥጋ የሚተላለፉ በሽታዎች፤** በእንግሊዝኛው ምኅፃረ ቃል (STI—Sexually Transmitted Infection) የሚባሉት እንደ ቂጥኝ፣ ጨብጥ፣ ከርክርና ባምቡሌ ያሉትን የሚያካትት ነው:: እንዲሁም ከእነዚህ ሌላ በግብረ ሥጋ እንደሚተላለፉ የታወቁትን በሽታዎች ሁኔታ ይጨምራል::

**የሥራ ውል መቋረጥ፤** ይህ ቃል የዓለም ሥራ ድርጅት በ1982 የሥራ ውልን መቋረጥ አስመልክቶ ባወጣው ድንጋጌ (ቁ. 158) ውስጥ የተሰጠውን ትርጉም እንደ ያዘ ያገለግላል:: ይኸውም በአሠሪው ፍላጎት ሠራተኛውን ማሰናበት ነው::

**ጠቅላላ ጥንቃቄዎች፤** በደም ሴሎች (ፓቶጂንስ) ውስጥ በመሆን በቀላል ደረጃ የሚታዩ በሽታዎችን ችግር የመቆጣጠር ልምድ:: (ሙሉ ማብራሪያውን በአባሪ 2 ተመልከት)

**መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች** *(እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ በመባል ይታወቃል)*፤ ይህ ቃል በአባሪ 1 ተብራርቶአል::

**የሠራተኞች ተወካዮች፤** የዓለም ሥራ ድርጅት በ1971 ባወጣው የሠራተኞች ተወካዮች ድንጋጌ (ቁ. 135) ውስጥ እንደ ተገለጸው በብሔራዊ ሕግና መመሪያ መሠረት የሠራተኞች ተወካዮች ሲባል:-

ሀ. የሠራተኛ ማኅበራት ተወካዮች፣ ማለትም በእነዚህ ማኅበራት ወይም በአባላቱ የተሰየሙ ወይም የተመረጡ፤ ወይም

ለ. ተመራጭ ተወካዮች፤ ማለትም በብሔራዊ ሕግ፣ ወይም መመሪያ፣ ወይም የኅብረት ስምምነቶች መሠረት በድርጅቱ ሠራተኞች በነፃ የተመረጡና እንቅስቃሴዎቻቸው ባሉበት አገር የሠራተኛ ማኅበራት እንደ ልዩ መብት የታወቁ ተግባሮች ናቸው::

**ተጎጂነት፤** በማኅበራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መዳከምና ባህላዊ ጭብጥ፤ ሠራተኛውን ለበሽታ አደጋ ይበልጥ የሚያጋልጡ የሥራ ሁኔታዎችና ልጆችን ያለ ዕድሜያቸው ወደ ሥራ የማሰማራት አደጋን ያመለክታል:: (ለበለጠ ማብራሪያ በአባሪ 1 ተመልከት)

# 4. ቁልፍ መርሆዎች

## 4.1. ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የሥራ ቦታ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ/ማወቅ

ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የሥራ ቦታ ጥያቄ ነው፤ ከዚህም የተነሣ እንደ ማንኛውም በሥራ ቦታ እንደሚያጋጥም አሳሳቢ ህመም/ሁኔታ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል:: ይህም የሠራተኛውን ኃይል ስለሚያጠቃ ብቻ ሳይሆን የሥራ ቦታ የማኅበረሰቡ አካል እንደ መሆኑ መጠን የወረርሽኙን ስርጭትና ውጤቶቹን ለመግታት በሚደረገው ትግል የሚጫወተው ሚና ስላለው ነው::

## 4.2. መድልዎ አልባነት

በአመርቂ ሥራ መንፈስና በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የታመሙና የተጠቁ ሰዎችን መብትና ሰብአዊ ማንነት በማክበር አንፃር በበሽታው በተጠቁትም ሆነ በሚገመቱት ሠራተኞች ላይ ምንም መድልዎ ሊኖር አይገባም:: ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደረግ መድልዎና የተዛባ አመለካከት ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ለመከላከል የታለመውን ጥረት ያሰናክላል::

## 4.3. የፆታ እኩልነት

ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በተመለከተ የፆታ ልዩነቶች በራሳቸው ሊታወቁ ይገባል:: ከተፈጥሮአዊ፣ ማኅበራዊ-ባህላዊ እና ኤኮኖሚያዊ ምክንያቶች የተነሣ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ወረርሽን ለመያዝና በበለጠ ክፉኛ ለመጠቃት የተጋለጡ ናቸው:: በማኅበረሰቦች ውስጥ ባለው የፆታ ልዩነት ስፋት፣ አድልዎና የሴቶች ዝቅተኛነት መጠን በአፍራሽ መልኩ በኤች.አይ.ቪ. የመያዛቸው እድል የሰፋ እንዲሆን ያደርገዋል:: ስለዚህ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የፆታ ግኝኙነትና የሴቶችን አቅም ማጐልበት የኤች.አይ.ቪ.ን በሽታ መስፋፋት በአጥጋቢ ሁኔታ ለመከላከልም ሆነ ሴቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በተሳካ ሁኔታ እንዲቋቋሙት ለማስቻል በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው::

## 4.4. ጤናማ የሥራ አካባቢ

ጤንነትንና ደህንነትን በተመለከተ የ1981 የዓለም ሥራ ድርጅት ድንጋጌ ቁጥር 155 መሠረት በሚመለከታቸው ሁሉ ዘንድ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የሥራ አካባቢዎች ኤች.አይ.ቪ.ን ለመከላከል በሚያስችል መልኩ ጤናማና አስተማማኝ መሆን አለባቸው::

ጤናማ የሥራ አካባቢ ሠራተኞች በአካልና በአእምሮ ጤናነት አንፃር ችሎታቸውን በበለጠ ተገባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻችላቸዋል::

## 4.5. ማኅበራዊ ውይይት

ስኬታማ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲና ፕሮግራም ተገባራዊነት በአሠሪዎች፣ በሠራተኞችና በተወካዮቻቸው እንዲሁም በመንግሥት መካከል ትብብርና መተማመን ይጠይቃል፤ ተገቢ በሚሆንበት ጊዜም በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የተያዙና የተጠቁ ሰዎችን ንቁ ተሳትፎ ያካትታል።

## 4.6. ከቅጥርና ከሥራ ሂደቶች ለማግለል ሲባል የሚደረግ ምርመራ

በሥራ ለመቀጠር የሚያመለክቱና በሥራ ላይ ያሉ ሰዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ምርመራ እንዲያደርጉ ሊገደዱ አይገባም።

## 4.7. ምሥጢራዊነት

ለሥራ የሚያመለክቱ ሰዎች ወይም ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ. ጋር በተያያዘ መልኩ ያላቸውን የግል መረጃ ይፋ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ ሁኔታ የለም። ሠራተኞች የሥራ ባለደረቦቻቸውን የግል መረጃዎች እንዲሰጡ ሊገደዱ አይገባም። የአንድ ሠራተኛ የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ የያዙ መረጃዎችን ማግኘት የሠራተኞችን የግል መረጃ ስለ መጠበቅ በ1997 ከወጣው የዓለም ሥራ ድርጅት መመሪያ ጋር በሚስማማ የምሥጢራዊነት ሕግ የተገደበ መሆን አለበት።

## 4.8. የቅጥር ግኙኙነት ቀጣይነት

የኤች.አይ.ቪ. በሽታ ቅጥርን ለማቋረጥ ምክንያት አይሆንም። በሌሎች ሁኔታዎች እንዳለው ሁሉ ከኤች.አይ.ቪ ጋር በተያያዘ መልኩ ህመም ያለባቸው ሰዎች ጤናቸው እስከፈቀደ ድረስ ተስማሚ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው መሥራት መቻል አለባቸው።

## 4.9. መከላከል

የኤች.አይ.ቪ. በሽታን መከላከል ይቻላል። የመተላለፊያ መንገዶቹን የመከላከል ግብ መምታት የሚቻለው ከብሔራዊ ሁኔታዎች ጋር የተስማሙና ከባህላዊ ጥንቃቄዎች ጋር የተዛመዱ ስልቶችን በመቀየስ ነው።

የመከላከሉ ጥረት የጠባይ ለውጥ በማምጣት፣ በእውቀት፣ በህክምናና መድልዎ የሌለበት ሁኔታ በመፍጠር ሊደገፍ ይችላል።

ማኅበራዊ አጋሮች የመከላከሉን ጥረቶች ለማሳደግ፣ በተለይ የአቋምና የጠባይ ለውጥ በማምጣት፣ ማኅበራዊና ኤኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መረጃና ትምህርት ለማስፋፋት በሚካሄዱ ጥረቶች ውስጥ የተለየ ቦታ አላቸው፡፡

## 4.10. እንክብካቤና ድጋፍ

አንድነት፣ እንክብካቤና ድጋፍ በሥራው ዓለም ለኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ለሚሰጠው ምላሽ አቅጣጫ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ሠራተኞች ሁሉ፣ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የሚኖሩ ሠራተኞችን ጨምሮ፣ በአቅማቸው ህክምና የማግኘት መብት አላቸው፡፡ ከማኅበራዊ ዋስትና ሕጎች፣ ፕሮግራሞችና ሙያዊ ሥልጠናዎች የሚመነጩ ጥቅሞችን በማግኘቱ ረገድ በእነርሱና በጥገኞቻቸው ላይ መድልዎ ሊደረግባቸው አይገባም፡፡

# 5. ጠቅላላ መብቶችና ኀላፊነቶች

## 5.1. መንግሥታትና ኀላፊነት የተሰጣቸው ባለሥልጣኖቻቸው

ሀ. ***መጣጣም፤*** *መንግሥታት የሥራውን ዓለም በብሔራዊ እቅዶች ውስጥ ማካተት ያለውን አስፈላጊነት በመገንዘብ በብሔራዊ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ አቅዶችና ፕሮግራሞች የሚኖረውን መጣጣም ማረጋጥ አለባቸው፡፡ ይኸውም ለምሳሌ ብሔራዊ የኤይድስ ምክር ቤት በማዋቀሩ ሂደት አሠሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችንና ለሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳዮች ተጠያቂ የሆኑ ሚኒስቴሮች እንደ ተካተቱ በማረጋገጥ ይሆናል፡፡*

ለ. ***ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ፤*** *የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ለጥበቃና ለመከላከል እንዲረዳ ሰፋት ያላቸውን አጋሮች ሊያንቀሳቅሱና እገዛ ሊሰጡ ይገባል፤ ይኸውም በሥራው ዓለም ያሉትን አጋሮች እንዲያካትት ሆኖ መንግሥታዊ ድርጅቶችን፣ የግሉን ዘርፍ፣ የሠራኞችና የአሠሪዎች ማኅበራትን፣ እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን አጋሮች ሁሉ ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡*

ሐ. ***ቅንጅት፤*** *አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር እንዲቻል በኤይድስ ላይ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በብሔራዊ ደረጃ መቀናጀት የሚገባቸው ሲሆን ይህም አግባብነት ባላቸው አጋሮች (አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ሌሎች) ላይ ማተኮር ይኖባቸዋል፡፡ ቅንጅቱ ቀደም ሲል ባሉ የድጋፍ አገልግሎቶች ላይ የተገነባ መሆን አለበት፡፡*

መ. ***መከላከልና ጤናን ማሳደግ፤*** *ኀላፊነት ያላቸው ባለሥልጣኖች በሥራ አካባቢ ግንዛቤንና የመከልከል ፕሮግራሞችን ለማሳደግ ማኅበራዊ አጋሮችን ሊያነሣሡና ከእነርሱም ጋር በአንድነት ሊሠሩ ይገባል፡፡*

ሠ. ***የህክምና መመሪያ፤*** አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ባላቸው አገሮች ውስጥ መንግሥታት ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የህክምና አያያዝና እንክብካቤውን በተመለከተ አሠሪዎችን ለመደገፍ መመሪያዎች ሊያቀርቡላቸው ይገባል:: እነዚህ መመሪያዎች ያሉትን አገልግሎቶች ትኩረት ውስጥ ማስገባት አለባቸው::

ረ. ***ማኅበራዊ ጥበቃ፤*** መንግሥታት ሌላ ከባድ ህመም ካለባቸው ሠራኞች ባላነሰ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በሽተኞችም ተመሳሳይ ጥቅሞችን ማግኘት እንዲችሉ በብሔራዊ ሕጎችና ደንቦች ማረጋገጥ አለባቸው:: የማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችን በመዘርጋቱና ተገባራዊ በማድረጉ ረገድ መንግሥታት የህመሙን ከጊዜ ወደ ጊዜ የመቀያየር ባሕርይ ግምት ውስጥ ማስገባትና እንደ ሁኔታውም ፕሮግራሞችን ማስተካከል አለባቸው፤ ይኸውም ለምሳሌ እንዳስፈላጊነቱ ጥቅሞችን በማቅረብና ለጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት ነው::

ሰ. ***ምርምር፤*** በብሔራዊ የኤይድስ እቅዶች ጋር መጣጣምን ለማረጋገጥ፣ ማኅበራዊ አጋሮችን ለማንቀሳቀስ፣ በሥራ ቦታዎች የወረርሽኙን ወጪ ለመገምገም፣ ለማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓትና ለኤኮኖሚ፤ እንዲሁም ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ተጽእኖዎችን ለማለዘብ፣ ዕቅዶችን ለማመቻቸት ኀላፊነት ያላቸው ባለሥልጣኖች የሥነ-ሕዝብ ትንበያዎችን፣ እንቅስቃሴና ጥረት፣ እንዲሁም ስለ በሽታው ስፋትና ክስተት ጠቃሚ ልምዶችን በማሳተሙ ረገድ ማበረታትና ማገዝ ይኖርባቸዋል:: ይህን ለማረጋገጥ መንግሥታት ድርጅታዊ የቁጥጥር ሥርዓትን ለመዘርጋት ጥረት ማድረግ አለባቸው:: ምርምሩ ከአሠሪዎችና ከማኅበሮቻቸው፣ እንዲሁም ከሠራተኞችና ከማኅበሮቻቸው ጥናትና መረጃ የሚጠቀም፣ የፆታ ጥያቄ ትንተናዎችን ያካተተ ሊሆን ይገባል:: እስከ ተቻለ ድረስ መረጃ አሰባሰቡ በሴክተር ላይ ያተኰረ ሆኖ በፆታ፣ በዘር፣ በፆታዊ አመለካከት፣ በእድሜ፣ በቅጥር፣ በሙያዊ ሁኔታ ለባህላዊ ልምዶች ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል:: በሚቻልበት ቦታ ተጽእኖዎችን ለመዳሰስ የሚያስችሉ ቋሚ ዘዴዎች መኖር ይገባቸዋል::

ሸ. ***የገቢ ምንጭ፤*** መንግሥታት በሚቻልበት ቦታ ከማኅበራዊ አጋሮችና አግባብነት ካላቸው ሁሉ ጋር በመመካከር ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ሊያስከትል የሚችለውን ወጪ ሊገምቱና ለብሔራዊ የኤይድስ ስልታዊ እቅዳቸው ማስፈጸሚያ፣ አስፈላጊ በሆነበት ቦታም ለማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓታቸው የሚሆን ከአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ የገንዘብ እርዳታ ሊፈልጉና ሊያንቀሳቅሱ ይገባል::

ቀ. ***ሕግ ማውጣት፤*** በሥራ ቦታ የሚደረገውን መድልዎ ለመቅረፍ፣ ለመከላከልንና ማኅበራዊ ጥበቃን ለማረጋገጥ፣ መንግሥታት ከማኅበራዊ አጋሮችና በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመመካከር አግባብነት ያለው የቁጥጥር ሥርዓት ሊያዘጋጁና እንዳስፈላጊነቱም የሠራተኛ ሕጎቻቸውንና ሌሎች ድንጋጌዎችን ማስተካከል ይገባቸዋል::

በ. ***የመንግሥትን ድጋፍ ለማግኘት የሚታዩ መስፈርቶች፤*** መንግሥታት ለብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መነሻ ገንዘብና ማበረታቻ በሚሰጡበት ጊዜ ተቀባዮቹ ለብሔራዊ ሕጎች ተገዢ እንዲሆኑ መጠየቅና ይህን መመሪያ ተገባራዊ የሚያደርጉበትን ፖሊሲዎችና ደንቦች እንዲያከብሩ ማበረታታት አለባቸው::

ተ. ***ተፈጻሚነት፤*** *ኀላፊነት ያላቸው ባለሥልጣኖች፣ በሥራው ዓለም አሠሪዎች ሆኑ ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን የሚመለከቱ ደንቦችና ድንጋጌዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማክበር እንዲችሉ ቴክኒካዊ መረጃና ምክር ማቅረብ አለባቸው። እንደ ማምረቻና ሥራ ቁጥጥሮችና የሥራ ክርክር ችሎቶች ያሉትን የማስፈጸሚያ መዋቅሮችና ሥርዓቶችን ማጠናከር ይኖርባቸዋል።*

ቸ. ***መደበኛ ባልሆነ ሥራዎች የተሰማሩ ሠራተኞች*** *(እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ በመባል ይታወቃል)፤ መንግሥታት እንዲህ ላሉት ሠራተኞች የገቢ ምንጭና ማኀበራዊ ደህንነትን ጨምሮ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መከላከል ፕሮግራሞች እንዲደርሳቸው ማድረግ አለባቸው። እንዲሁም ተገቢ በሚሆንበት ቦታ የአካባቢውን ማኀበረሰብ በመጠቀም መንግሥታት አዳዲስ አቀራረቦችን ሊነድፉና ሊያጐለብቱ ይገባል።*

ኀ. ***ትኩረት፤*** *መንግሥታት በሕዝብ ጤና ጥበቃ ፕሮግራሞች፣ በማኀበራዊ ዋስትና አሠራሮች እና/ወይም አግባነት ባላቸውና በመንግሥት ተነሣሽነት በሚካሄዱ እንቅስቃዎች አማካይነት እንክብካቤንና ድጋፍን ማሳደግ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም መንግሥታት የህክምና መገኘትን ለማረጋገጥ መጣርና ተገቢ በሚሆንበትም ቦታ ከአሠሪዎችና ከሠራተኞች ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራት ይኖርባቸዋል።*

ነ. ***ሕፃናትና ወጣቶች፤*** *መንግሥታት የሕፃናትን በሥራ ማሰማራት ለማጥፋት በሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ውስጥ ወላጃቸው ወይም ወላጆቻቸው በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በታመሙ ወይም በሞቱ ሕፃናትና ወጣቶች ላይ ወረርሽኙ የሚያሳደረው ተጽእኖ ግምት ውስጥ መግባቱን ማረጋገጥ አለባቸው።*

ኘ. ***አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብር፤*** *መንግሥታት በሥራው ዓለም ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስና ተዛማጅ ጥያቄዎች ዓለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኙ፣ በአህጉራዊ በዓለም አቀፋዊ ደረጃና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና አግባብነት ባላቸው አካሎች መካካል ትብብርን ማጐልበትና መደገፍ ይኖርባቸዋል።*

አ. ***ዓለም አቀፍ እገዛ፤*** *ተገቢ በሚሆንበት ቦታ መንግሥታት ለብሔራዊ ፕሮግራሞች የዓለም አቀፍ እገዛዎችን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል። የእድሜ ማራዘሚያ* (Antiretroviral—*አንቲሪትሮቫይራል) መድኃኒቶች ዋጋ እንዲቀንስና በቀላሉ ማግኘት እንዲቻል የሚካሄዱትን ጥረቶች ማበረታታት ይኖርባቸዋል።*

ከ. ***ተጎጂነት፤*** *መንግሥታት በበሽታው በበለጠ ተጠቂ የሆኑ ሠራተኞችን ለመለየት እርምጃ መውሰድና ለመጋለጥ የሚዳርጓቸውን ምክንያቶች ለማስወገድ ስልቶችን ማውጣት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም መንግሥታት ለእነዚህ ሠራኞች ተገቢ የመከላከል ፕሮግራሞች እንዲኖሩ ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።*

## 5.2. አሠሪዎችና ማኅበሮቻቸው

ሀ. ***የሥራ ቦታ ፖሊሲ***፤ አሠሪዎች የወረርሽኙን መስፋፋት ለመከላከልና ከቫይረሱ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚደረገውን መድልዎ ለመከላከል የታቀደ ተገቢ ፖሊሲን ለመተግበርና ለማሳደግ ከሠራተኞችና ከተወካዮቻቸው ጋር መመካከር ይኖርባቸዋል:: የሥራ ቦታ ፖሊሲ እቅድና ተግባራዊነት ማጣቀሻ በአባሪ 3 ይገኛል::

ለ. ***ብሔራዊ፣ የዘርፍና የሥራ ቦታ/ኢንተርፕራይዝ ስምምነቶች***፤ አሠሪዎች ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጥያቄዎች ከሠራተኞቻቸውና ከተወካዮቻቸው ጋር በሚደረግ ድርድር ለብሔራዊ ሕግና መመሪያ ተገዢ መሆን የሚገባቸው ሲሆን፤ በብሔራዊ፣ በዘርፍና በሥራ ቦታ/ኢንተርፕራይዝ ስምምነቶች ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጥበቃና መከላከል ዝግጅቶችን ለማካተት መጣር ይኖርባቸዋል::

ሐ. ***ትምህርትና ሥልጠና***፤ አሠሪዎችና ማኅበሮቻቸው ከሠራተኞችና ከተወካዮቻቸው ጋር በመመካከር በሥራ ቦታዎቻቸው ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ለመከላከል፣ ለጥበቃና ድጋፍ ለመስጠት፣ ለማስተማርና ለማሠልጠን እንዲሁም በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በተያዙ ወይም በተጠቁ ሰዎች ላይ የሚደረገውን መድልዎ ለመቀነስ፣ እነዚህም ለልዩ የአባልነት ጥቅሞችና መብቶች እርምጃዎችን ለመውሰድ ፕሮግራሞችን ማመንጨትና መደገፍ ይኖርባቸዋል::

መ. ***ኤኮኖሚያዊ ተጽእኖ***፤ አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው በዘርፋቸውና በሥራ ቦታ ላይ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ለሚያሳድረው ኤኮኖሚያዊ ተጽእኖ በትክክል ምላሽ ለመስጠት ተገቢ የአሰሳ ስልቶች መንደፍ ይኖርባቸዋል::

ሠ. ***የሠራተኛ አስተዳደር***፤ አሠሪዎች በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በተያዙ ወይም በተጠቁ ሰዎች ላይ መድልዎ የሚያደርግ ማንኛውም የሠራተኛ ፖሊሲ ወይም አሠራር ውስጥ መግባት የለባቸውም ወይም ሊፈቅዱ አይገባም:: በተለይም አሠሪዎች:-

- በዚህ መመሪያ ክፍል 8 እንደ ተዘረዘረው ካልሆነ በቀር ለኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ምርመራ ወይም ማጣራት ማስገደድ የለባቸውም፤
- በተገመተ ወይም በትክክለኛ ኤች.አይ.ቪ. ላይ ከተመሠረተ መድልዎና ጎጂ አመለካከት (stigmatization) ነፃ ሆኖ መከናወኑን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- ከኤች.አይ.ቪ ጋር የሚኖሩ ወይም ከኤይድስ ጋር የተያያዘ ህመም ያለባቸው ሰዎች መሥራት መቻላቸው በሕክምና እስከ ተረጋገጠ ድረስ እንዲሠሩ ማበረታታት አለባቸው::
- ከኤይድስ በተያያዘ ሁኔታ በጣም የታመመ ሠራተኛ ሥራውን ለመቀጠል ካልቻለና የተራዘመ ፈቃድን ጨምሮ አማራጭ የሥራ ሁኔታን ማመቻት ካልተቻለ በጸረ መድልዎና በሠራተኛ ሕጎች መሠረት፣ እንዲሁም የአሠራር ሥርዓትና ሙሉ መብትን ባከበረ መልኩ የሥራ ውሉን ማቋረጥ ይቻላል::

ረ. ***ቅሬታና የዲሲፕሊን ሥርዓቶች***፤ አሠሪዎች ከሥራ ጋር ለተያያዙ ቅሬታዎች ሠራኞችና ተወካዮቻቸው ሊገለገሉባቸው የሚችሉ የአሠራር ሥርዓቶች ሊኖሩአቸው ይገባል:: እነዚህ ሥርዓቶች በተገመተ ወይም በትክክለኛ የኤች.አይ.ቪ

ሁኔታ ላይ መድልዎ በሚያደርግ፣ ወይም የሥራ ቦታን የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲ በሚጥስ ማንኛውም ሠራተኛ (አሠሪ) ላይ የሚቀርቡ የዲሲፕሊን ክሶች በምን ሁኔታ ላይ ተመሥርተው መቅረብ እንዳለባቸው መዘርዘር አለባቸው::

ሰ. ***ምሥጢራዊነት***፤ ከቫይረሱ ጋር የተያያዙ የሠራተኞች መረጃዎች በጥብቅ ምሥጢርነት ሊጠበቁና በህክምና ፋይል ውስጥ ብቻ ሊቀመጡ ይገባል፤ እነዚህን ማግኘት የሚቻለው ከ1985ቱ የዓለም ሥራ ድርጅት የሙያ ጤና አገልግሎት መሪ ሃሳብ (ቁ. 171) ጋር በሚስማማ መልኩ እና በብሔራዊ ሕጎችና ልምዶች መሠረት መሆን ይኖርበታል:: እንደዚህ ያሉትን መረጃዎች የማግኘቱ ሁኔታ ለጤና መኰንኖች በጥብቅ መወሰን የሚገባው ከመሆኑ ሌላ በሕግ ከተጠየቀ ወይም በሚመለከተው ግለሰብ ስምምነት ከተገኘ ብቻ መሆን አለበት::

ሸ. ***አደጋን መቀነስና ቁጥጥሩ***፤ አሠሪዎች ነፃና ጤናማ የሥራ አካባቢ እንዲኖርና እንዲሁም ተግባራዊ እንዲሆን፣ ለምሳሌ መከላከያ መሣሪያዎችን ማቅረብና መጠገን፣ የመጀመሪያ እርዳታ መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል:: ግለሰቦች የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ ለመደገፍ አሠሪዎች ተገቢ በሚሆንበት ቦታ የወንድና የሴት ኮንዶሞች ማቅረብ፣ የምክር አገልግሎት መስጠት፣ እንክብካቤና እገዛ ማድረግ፣ እንዲሁም ወደ ከፍተኛ ህክምና የማስተላፍ (ሪፈራል) አገልግሎት መስጠት ይኖርባቸዋል:: የችግሩ ስፋትና ወጪ አዳጋች በሚሆንበት ጊዜ አሠሪዎች እና/ወይም ማኅበሮቻቸው ከመንግሥት ወይም አግባብነት ካለው ተቀዋም እርዳታ መፈለግ ይኖርባቸዋል::

ቀ. ***ሠራተኞች ከሰው ደምና ከሰውነት ፈሳሽ ጋር መደበኛ ግኙኙነት የሚያደርጉባቸው የሥራ ቦታዎች***፤ እንደዚህ ባሉት የሥራ ቦታዎች ሠራኞች ሁሉ በጠቅላላ ጥንቃቄዎች (Universal Precautions) መሠልጠናቸውን፣ እንዲህ ያለ ሙያዊ አጋጣሚ በሚከሰትበት ጊዜ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች ሁልጊዜ ስለ መጠበቃቸው፣ ስለሚከተሉት ሂደቶች እንደሚያውቁ ለማረጋገጥ አሠሪዎች ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ይፈለግባቸዋል:: ለእነዚህ እርምጃዎች መሣሪያዎች መቅረብ አለባቸው::

በ. ***በአቅም ያለውን ስለ መቻል***፤ አሠሪዎች ከሠራተኞችና ከማኅበሮቻቸው ጋር በመመካከር ከኤች.አይ.ቪ. ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለታመመ ሠራተኛ ሁኔታዎችን ለእርሱ ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ለማመቻቸት እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል:: ይህም የሥራ ሰዓትን ማስተካከልን፣ የተለዩ መሣሪያዎችን ማቅረብ፣ ለእረፍት እድል መስጠትን፣ ለህክምና ቀጠሮዎች ፈቃድ መስጠትን፣ ተቀያያሪ የህመም ጊዜ ፈቃድን፣ ከፊል የሥራ ሰዓትና ወደ ሥራ የመመለስ ማስተካከያዎችን ይጨምራል::

ተ. ***ቅስቀሳ (Advocacy)***፤ በጥሩ የዜግነት መንፈስ አሠሪዎችና ማኅበሮቻቸው፣ ተገቢ በሚሆንበት ቦታ፣ በሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ለመከላከልና የቁጥጥር አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ እንደ እነርሱ አሠሪ የሆኑ አቻዎቻቸውን ማበረታት ይኖርባቸዋል:: መንግሥታትም የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መስፋፋት ለማቆምና ተፅእኖውን ለማለዘብ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ እንዲወስዱ ማበረታት አለባቸው:: እንደ ንግድ ማኅበር የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ካውንስሎች ያሉ ሌሎች አጋሮች ለሂደቱ ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ::

ቸ. ***በምሥጢር ለሚካሄድ የኤች.አይ.ቪ. የምክር አገልግሎትና ምርመራ ስለሚሰጥ እገዛ***፤ *አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ተወካዮቻቸው በሠለጠኑ የጤና አገልግሎቶች የሚቀርቡ በፈቃደኛነት ላይ ለተመሠረተ ምሥጢራዊ የምክር አገልግሎትና ምርመራ የሚደረገውን ድጋፍ ማበረታታት አለባቸው፡፡*

ኀ. ***መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች፣*** *(እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ በመባል ይታወቃል)፤ መደበኛ ባልሆኑ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ለሚሠሩ ሠራተኞች አሠሪዎች ስለ መከላከልና እንክብካቤ ጥናት ማካሄድና አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ ፕሮግራሞችን መዘርጋት ይኖባቸዋል፡፡*

ነ. ***ዓለም አቀፍ አጋርነት፤*** *አሠሪዎችና ማኅበሮቻቸው ተገቢ በሚሆንበት ቦታ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ላይ በሚካሄደው የዓለም አቀፍ አጋሮች ጥረት ውስጥ አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው፡፡*

## 5.3. *ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው*

ሀ. ***የሥራ ቦታ ፖሊሲ፤*** *ሠራኞችና ተወካዮቻቸው በሥራ ቦታቸው የወረርሽኙን መስፋት ለመከላከልና ሠራተኞችን ሁሉ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በተገኛኘ መልኩ ከሚደረግ መድልዎ ለመጠበቅ የተነደፈ ተገቢ ፖሊሲ ተግባራዊ ስለማድረግ ከአሠሪዎቻቸው ጋር ሊመካከሩ ይገባል፡፡ የሥራ ቦታ ፖሊሲ እቅድና ተግባራዊነት ማጣቀሻ በአባሪ 3 ይገኛል፡፡*

ለ. ***ብሔራዊ፣ የዘርፍና የሥራ ቦታ/ኢንተርፕራይዝ ስምምነቶች፤*** *ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ስለ ቅጥር ስምምነቶችና ሁኔታዎች በሚደራደሩበት ጊዜ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር በተዛመደ መልኩ ስለሚነሡ ጥያቄዎች ለብሔራዊ ሕጎችና ልምዶች ተገዢ መሆን፣ እንዲሁም የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጥበቃና መከላከል በተመለከተ የብሔራዊ፣ የዘርፍና የሥራ ቦታ/ኢንተርፕራይዝ ስምምነቶች በድንጋጌዎቹ ይዘት ውስጥ እንዲካተቱ መጣር ይኖርባቸዋል፡፡*

ሐ. ***መረጃና ትምህርት***፤ *ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው በሥራ ቦታቸው ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መረጃ ለማቅረብ ባሉት የማኅበራት መዋቅሮች፣ በሌሎች ተቅዋሞችና ዘዴዎች ሊጠቀሙ፣ እንዲሁም ስለ ሠራተኞች መብቶችና ጥቅሞች በመደበኛ ሁኔታ የሚሻሻሉ መረጃዎችን ጨምሮ ለሠራተኞችና ለቤተሰቦቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ትምህርታዊ ቁሳቁሶችና እንቅስቃሴዎችን ማሳደግ ይኖርባቸዋል፡፡*

መ. ***ኤኮኖሚያዊ ተጽእኖ፤*** *ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በተለይ በሥራ ቦታቸውና ዘርፋቸው የሚያሳድረውን ኤኮኖሚያዊ ተጽእኖ ለመዳሰስና ምላሽ ለመስጠት ስለሚነድፉአቸው ስልቶች ከአሠሪዎቻቸው ጋር በኅብረት መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡*

ሠ. ***ቅስቀሳ (advocacy)፤*** ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መከላከልና ቁጥጥር ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ ከአሠሪዎቻቸውና ከማኅበሮቻቸው፣ እንዲሁም ከመንግሥታት ጋር በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል።

ረ. ***የሠራተኞች አስተዳደር ፖሊሲዎች፤*** ሠተራኞችና ተወካዮቻቸው ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር በሚኖሩ ሠራተኞች ላይ መድልዎ የማያደርግ የሠራተኛ አስተዳደር ፖሊሲና ልምዶች በመፍጠር ረገድ አሠሪዎቻቸውን ሊያበረታቱና ድጋፍ ሊሰጡአቸው ይገባል።

ሰ. ***የተገዢነት ክትትል፤*** ሠራተኞችና ተወካዮቻቸው በሥራ ቦታቸው የሚፈጠሩትን ጉዳዮች በቅሬታና በዲሲፕሊን የአቀራረብ ሥርዓት ጥያቄዎችን የማንሣት መብት አላቸው፤ እንዲሁም/ወይም በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ መድልዎን ሁሉ ለሚመለከታቸው ሕጋዊ የሥልጣን አካላት ማመልከት ይገባቸዋል።

ሸ. ***ሥልጠና፤*** የሠራተኞች ማኅበራት ስለ ወረርሽኙ ለሚነሡ ጥያቄዎች፣ ስለ ተገቢ መልሶች፣ እንዲሁም ከቫይረሱ ጋር ስለሚኖሩ ሰዎች ጠቅላላ ፍላጎትና ስለሚደረግላቸው እንክብካቤ የሥልጠና ኮርሶችን በሥራ ቦታዎች መፍጠርና ማካሄድ ይኖርባቸዋል።

ቀ. ***አደጋን መቀነስና ቁጥጥር፤*** ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው የመከላከያ መሣሪያና የመጀመሪያ እርዳታ ትክክለኛ አጠቃቀምና አጠባበቁን ጨምሮ ለነፃና ጤናማ የሥራ አካባቢ መኖር አሠሪዎቻቸውን ሊደግፉና ከእነርሱም ጋር ሊተባበሩ ይገባቸዋል። ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው የሥራ አካባቢ ተጎጂነትን ሊገመግሙና እንዳስፈላጊነቱ በሠራተኞች ላይ ያተኮሩ ፕሮገራሞችን መፍጠር ይኖርባቸዋል።

በ. ***ምሥጢራዊነት፤*** ሠራተኞች የራሳቸውን የህክምና ፋይሎች የማግኘት መብት አላቸው። የሠራተኞች ማኅበራት ስለ አንድ ሠራተኛ ኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አይችሉም። በሁሉም ሁኔታዎች የሠራተኛ ማኅበራት ኃላፊነቶችና እንቅስቃሴዎች በሚተገበሩበት ጊዜ የምሥጢራዊነት ሥርዓቶችና የሚመለከተው የግለሰብ ፈቃድ አስፈላጊነት በ1985ቱ የመደበኛ ጤና አገልግሎቶች መሪ ሃሳብ (ቁ. 161) በተቀመጠው መሠረት ተግባራዊ መሆን አለበት።

ተ. ***መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሠራተኞች*** *(እንዲሁም መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ በመባል ይታወቃል)፤* ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው አግባብነት ካላቸው ሌሎች አጋሮች ጋር በመተባበር እንቅስቃሴአቸውን ለእነዚህ ሠራተኞች ማዳረስ ይኖርባቸዋል።አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መስፋፋት ለመከላከልና ተጽእኖውን ለማለዘብ የሚፈጠሩ አዲስ ሃሳቦችን መደገፍ አለባቸው።

ቸ. ***ተጎጂነት፤*** ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው የህመሙን ተጠቂነት በተለዩ የሠራተኛ ክፍሎች ላይ የሚያባብሱት ጭብጦች እንዲተኮረባቸው ከአሠሪዎቻቸው ጋር በመመካከር ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ኀ. ***በፈቃደኛነት ለሚካሄድ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራና የምክር አገልግሎት የሚደረግ ድጋፍ፤*** ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ምሥጢራዊ የሆነ ፈቃደኛ ምርመራና የምክር አገልግሎትን እንዲያገኙ ለማበረታታትና ለመደገፍ ከአሠሪዎቻቸው ጋር በመተባበር ሊሠሩ ይገባል፡፡

ነ. ***ዓለም አቀፍ አጋርነት፤*** ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በሥራ ዓለም ለማጉላትና በሠራተኛ መብት ጥያቄ ዘመቻ ውስጥ እንዲካተት ለማድረግ ሠራተኞችና ማኅበሮቻቸው ከሀገር ውጭ የሚገኙትን አህጉራዊ፣ ዓለም አቀፋዊና የዘርፍ ቅንጅቶችን በመጠቀም የጋራ ግንባር መፍጠር ይኖርባቸዋል፡፡

# 6. በመረጃና በትምህርት የሚደረግ መከላከል

የወረርሽኙን መስፋፋት ለመዋጋትና ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ከሚኖሩ ሠራተኞች ጋር የበለጠ መቻቻልን ለማበረታታት የሥራ ቦታ የመረጃና የትምህርት ፕሮግራሞች መሠረታዊ ናቸው፡፡ ውጤታማ ትምህርት ሠራተኞች ራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ. በሽታ ለመጠበቅ ያላቸውን ችሎታ ለማሳደግ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የተያያዘ ሥጋትና ኅሊናን ጎጂ አነጋገሮችን (stigmatization) ይቀንሳል፣ በሥራ ቦታ ቀውስን ያሳንሳል፣ እንዲሁም የአቋምና የባሕርይ ለውጥ ያስገኛል፡፡ የከፍተኛ ደረጃ ድጋፍና የሚመለከታቸውን ሁሉ ሙሉ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ፕሮግራሞች በመንግሥት፣ በአሠሪዎች፣ በሠራተኞችና በማኅበሮቻቸው መካከል በሚደረግ ምክክር ሊፈጠሩ ይገባል፡፡ በተጻፈ ቃል ብቻ ሳይሆን መረጃና ትምህርት፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ የርቀት ትምህርትን ጨምሮ በተለያዩ መልኮች መቅረብ አለበት፡፡ ፕሮግራሞቹ በሥራ ቦታ በእድሜ፣ በፆታ፤ በፆታዊ አመለካከት፣ በየዘርፉ ጠባይና ባሕርይ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ሁኔታዎችና በባህላዊ ጭብጦች አኳያ የታለሙና የታቀዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡ እነዚህም በተከበሩና በታመኑ ግለሰቦች መሰጠት አለባቸው፡፡ በፕሮግራሞች ንድፍና ተግባራዊነት ውስጥ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ተሳትፎ ውጤታማ እንደ ሆነ ሁሉ በጓደኛ (በአቻ) የሚሰጥ ትምህርት የተለየ ውጤት አለው፡፡

## 6.1. መረጃና ግንዛቤን ከፍ ማድረግ ዘመቻዎች

ሀ. የመረጃ ፕሮግራሞች በሚቻልበት ቦታ ሁሉ በአንድ ክልል ከሚገኝ ማኅበረሰብ፣ በአካባቢ ወይም በአገር ውስጥ ካሉ ሰፋት ካላቸው የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ዘመቻዎች ጋር የተያያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ፕሮግራሞቹ ኤች.አይ.ቪ. እንዴት እንደሚተላለፍና እንደማይተላለፍ፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ዙሪያ ያሉትን አፈ-ታሪኮች የሚያስወግድ፣ ኤች.አይ.ቪን እንዴት መከላከል እንደሚቻል፣ ስለ ህመሙ የህምክና ገጽታ፣ ኤይድስ በግለሰቦች ላይ ስላለው ተጽእኖ፣ ስለ እንክብካቤ፣ ድጋፍና ህክምና ያለውን እድል በትክክል በሚያስረዱ አዲስ መረጃዎች ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. እስካሁን ተግባራዊ እንደ ሆነው ሁሉ የመረጃ ፕሮግራሞች፣ ኮርሶችና ዘመቻዎች በተጨባጭ የትምህርትና የሰው ኃይል ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች፣ በሙያዊ ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም በፀረ-መድልዎ እቅዶች የተቀናጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 6.2. ትምህርታዊ ፕሮግራሞች

ሀ. ትምህርታዊ ዕቅዶች በአሠሪዎች፣ በሠራተኞችና በተወካዮቻቸው፣ አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታም በመንግሥትና በሌሎች በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ትምህርት በቂ ልምድ የያዙ አግባብነት ባላቸው አጋሮች መካከል በሚደረግ መመካከር፣ በምክር አገልግሎትና በጥንቃቄ ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው፡፡ ዘዴዎቹ በተቻለ መጠን የሚያወያዩና የሚያሳትፉ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ክፍያ በሚታሰብበት የሥራ ሰዓቶችና ከሥራ ቦታ ውጭ ለሠተራኞች መገልገያ የሚሆኑ ትምህርታዊ ቁሳቁሶችን በማዳበሩ ረገድ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ኮርሶች በሚሰጡበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የተሳትፎ ቁጥጥር እንደ ሥራ ግዴታ ሊቆጠር ይገባል፡፡

ሐ. ተግባራዊና ተገቢ በሚሆንበት ቦታ ፕሮግራሞቹ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል፡-

- ግለሰቦች (እንደ ግለሰቦች ወይም እንደ አንድ ቡድን አባላት) በግል የሚያጋጥሙአቸውን አደጋዎች ለመገምገም የሚረዱ እንቅስቃሴዎችንና እነዚህን አደጋዎች ለመቀነስ ውሳኔ የመስጠት፣ የድርድርና የመገናኛ ብልሃቶችን፤ እንዲሁም የትምህርታዊ፣ የመከላከያና የምክር አገልግሎት ፕሮግራሞችን ማካተት፤
- በከፍተኛ ደረጃ አጋላጭ በሆኑ ባሕርዮችና ሌሎች የአደጋ ጭብጦች፣ ማለትም በሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ. በበለጠ ተጋላጭ ለሆኑ የሠራተኛ ክፍሎች ልዩ አጽንኦት መስጠት፤
- ኤች.አይ.ቪ. በመርፌ በሚወሰዱ መድኃኒቶች ወይም አደንዛዥ ዕፆች አማካይነት መተላለፍ መቻሉንና በዚህ መንገድ የሚተላለፈውን አደጋ ስለ መቀነስ መረጃ ማቅረብ፤
- በጐረቤት አገሮችና በአህጉራዊ ደረጃ በመንግሥት፣ በአሠሪዎችና በሠራተኞች ማኅበራት መካከል ውይይቶችን ማሳደግ፤
- ከሠራተኞች ማኅበራት ጋር በመተባበር በመንግሥታትና በኢንተርፕራይዞች በሚካሄዱ የሙያ ሥልጠናዎች ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ግንዛቤን ከፍ ማድረግ፤
- በወጣት ሠራተኞችና በሴቶች ላይ የተነጣጠሩ ዘመቻዎችን ማሳደግ፤
- ለሴቶች በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ተጎጂነትና ይህንን ተጎጂነት መቀነስ ለሚያስችሉ የመከላከል ስልቶች ልዩ ግምት መስጠት (*ክፍል 6.3 ተመልከት*)፤

- ኤች.አይ.ቪ. በድንገተኛ መነካካት ሊተላለፍ እንደማይችል፤ በኤች.አይ.ቪ. የተያዙ ሰዎች ሊገለሉና ሊዋረዱ እንደማይገባ፣ ይልቁን ሊደገፉና በሥራ ቦታ አስፈላጊ መመቻቸት ሊደረግላቸው እንደሚገባ ልዩ ግምት መስጠት፤

- የቫይረሱን ጎጂነት በመገንዘብ ሠራተኞች ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ የሥራ ባልደረቦቻቸው እንዲያዝኑና አድልዎ እንዳያደርጉ ማስረዳት፤

- ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ስለ ፈጠራቸው ሃሳቦችና ስሜቶች እንዲገልጹና እንዲወያዩ እድሉን መስጠት፤

- ሠራተኞች (በተለይ የጤና ጥበቃ ሠራተኞች) ስለ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች ማስተማርና ለበሽታው መጋለጥ በሚኖርበት ጊዜ መከተል ስለሚገባቸው ቅደም ተከተሎች መመሪያ መስጠት፤

- ከኤች.አይ.ቪ. ጋር ግንኙነት ስላላቸው ብቻ ሳይሆን ሁኔታዎቹ በህክምና ሊፈወሱ እንደሚችሉና በዚህም የሠራተኞችን ጤንነትና የሰውነት ውስጥ የመከላከል አቅምን ማሻሻል ስለሚቻል በግብረ ሥጋ ግንኙነት አማካይነት ስለሚተላለፉ በሽታዎችና ስለ ሳንባ ነቀርሳ መከላከልና ቁጥጥር ትምህርት ማቅረብ፤

- መደበኛ ጤና አጠባበቅና ተገቢ አመጋገብን ማሳደግ፤

- የወንድና የሴት ኮንዶሞችን አጠቃቀም ትምህርትን ጨምሮ ጤናማ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ልምድ ማዳበር፤

- የአቻ ትምህርትና መደበኛ ያልሆነ የትምህርት እንቅስቃሴዎችን ማበረታታት፤

- አስፈላጊ በሚሆንበት ቦታ  መገምገም፣ መመርመርና መስተካከል ይኖርበታል።

## 6.3. በፆታ ላይ ያተኮሩ ፕሮግራሞች

ሀ. ፕሮግራሞች ሁሉ ለፆታ ጉዳይ፣ እንዲሁም ለዘርና ለፆታዊ አመለካት ትኩረት የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህም ወንዶችና ሴቶችን በትክክል ዒላማ ማድረግ፣ ወይም የወንዶችና የሴቶች ሠራተኞችን የተለያየ የአደጋ ዓይነቶችና ደረጃዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ወንዶችን ሆነ ሴቶችን በተለያዩ ፕሮግራሞች ማቀፍን ያካትታል።

ለ. ለሴቶች የሚሰጡ መረጃዎች ከበሽታው እንዲጠነቀቁ፣ ለአደጋው መጋለጣቸው ከፍተኛ መሆኑን፣ በተለይ የወጣት ሴቶችን ልዩ ተጎጂነት፣ ማስረዳት አለባቸው።

ሐ. ትምህርት ወንዶችና ሴቶች በመካከላቸው ያለውን እኩል ያልሆነ የሥልጣን ግንኙነት እንዲገነዘቡና እርምጃ እንዲወስዱ ሊረዳቸው ይገባል፤ ማስፈራራትና ዓመፅ በልዩ ሁኔታ ሊተኮርባቸው ይገባል።

መ. ፕሮግራሞቹ በሥራ ቦታ ሆነ ከዚያ ውጭ መብታቸውን እንዲያውቁ የሚረዱና ራሳቸውን ለመጠበቅ ሥልጣን የሚሰጡአቸው መሆን አለባቸው።

ሠ. ለወንዶች የሚሰጠው ትምህርት ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን በመከላከል ረገድ የወንዶችን ኃላፊነት ለማሳደግ ግንዛቤን ከፍ ማድረግን፣ ጉዳትን መገምገምና ስልቶቹን ሊያካትት ይገባል።

ረ. ግብረ ሰዶም ፈጻሚ ለሆኑ ወንዶች ከእነዚህ ሠራተኞችና ከተወካዮቻቸው ጋር በመመካከር በትክክል የታቀዱ የመከላከል ፕሮግራሞች ሊፈጠሩ ይገባል።

## 6.4. ከጤና ማሳደግ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣም

ትምህርታዊ ፕሮግራሞች አመቺ በሚሆንበት ጊዜ ቁሳቁሶችን በተሳሳተ መንገድ መጠቀምን ድካምና የተዋለድ ጤና የሚመለከቱ ሥራዎች በሥራ ቦታ ጤናን ከማሳደግ ፕሮግራሞች ጋር መጣጣም ይኖርባቸዋል። ነባር የሥራ ቦታ መማክርት፣ ወይም የጤናና የደህንነት ኮሚቴዎች ለኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ግንዛቤ ዘመቻዎችና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች የመግቢያ ነጥብ ይሆናሉ። ይህ መጣጣም እየጨመረ የሄደውን ሱስ አስያዥ ዕፆችን በደም ሥር በተበከለ መርፌ መወጋት የሚያመጣውን የበሽታ ጉዳት ሊያጐላ ይገባል። እንዲሁም በአልኮልና በአደንዛዥ ዕፆች መስከር የኤች.አይ.ቪን በሽታ ጉዳት ሊያሳድግ ወደሚችል ጠባይ እንደሚመራ የሚያጎላ መሆን ይኖበታል።

## 6.5. የጠባይ ለውጥን ለመደገፍ የሚወሰዱ ተግባራዊ እርምጃዎች

ሀ. ሠራተኞች አደጋን በመቀነስ ረገድ ስላሉ ስልቶች ውጤት ያለው፣ ፍጹምና ወቅታዊ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፤ ተገቢ በሚሆንበት ቦታም የወንዶችና የሴቶች ኮንዶሞች አቅርቦት ሊኖር ይገባል።

ለ. በግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለሚተላለፉ በሽታዎች፣ ስለ ሳንባ ነቀርሳ ምርመራ፣ ህክምናና ቁጥጥር፣ እንዲሁም ከተውሳክ ስለ ጸዳ መርፌና ሲሪንጅ ልውውጥ ፕሮግራሞች፣ ወይም የት እንደሚገኙ ውጤታማ የሆነ የመረጃ አቅርቦት በቅድሚያ ሊኖር ይገባል።

ሐ. የገንዘብ እጥረት ላለባቸው ሴት ሠራኞች የሚሰጠው ትምህርት የአነስተኛ ገቢ ድጎማ፣ ለምሳሌ የገቢ ምንጭ ስለ መፍጠር እንቅስቃሴዎች፣ ከግብር ነፃ መሆንና የደመወዝ እገዛ መረጃ የማቅረብ ስልቶችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

## 6.6 ማኅበረሰብን የማስተማር ፕሮግራሞች

አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ተወካዮቻቸው በአካባቢ ማኅበረሰብ፣ በተለይ በትምህርት ቤቶች፤ የሚሰጠውን ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ስለ መከላከልና ቁጥጥር ፕሮግራሞች መረጃና ትምህርት ማበረታታትና ማሳደግ ይኖርባቸዋል። ሰዎች ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እድል ለመስጠትና ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች ብቸኝነታቸውንና መገለላቸውን በመቀነስ ደህንነታቸውን ለማሳደግ በማስተማሩ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ

ማበረታታት ይገባል። እንዲህ ያሉት ፕሮግራሞች ከተገቢ ብሔራዊና አካባቢ አካላት ጋር በመተባበር ሊካሄዱ ይገባል።

# 7. ሥልጠና

ሥልጠና ለተለያዩ ሠልጣኝ አካላት፣ ማለትም ለሥራ አስኪያጆች፣ ለተቆጣጣሪዎችና ለሠራተኛ ኃላፊዎች፣ ለሠራተኞችና ለተወካዮቻቸው፣ ለአሠልጣኝ አሠልጣኞች (ወንዶች ወይም ሴቶች)፣ ለአቻ አስተማሪዎች፣ ለመደበኛ የጤናና የደህንነት መኰንኖች፣ እንዲሁም ለማምረቻ/ሠራተኛ ተቆጣጣሪዎች የታቀደ፣ ተቀባይነት ያለው፣ መሆን አለበት። የዚህን ወጪዎች ለመክፈል ብልሃታዊ አቀራረቦች ሊፈለጉ ይገባል። ለምሳሌ ኢንተርፕራይዞች ከብሔራዊ የኤይድስ ፕሮግራሞች ወይም አግባብነት ካላቸው አጋሮች አስተማሪዎችን በመዋስ ወይም የራሳቸውን ሰዎች በማሠልጠን የውጭ እገዛ ሊፈልጉ ይችላሉ። የሥልጠና ቁሳቁሶቹ እንደ አቅርቦቱ መጠን በትልቁ ሊለያዩ ይችላሉ፤ እንደ አካባቢው ልማድና እንዲሁም የወንዶችና የሴቶች ሁኔታዎች ሊዋሃዱ ይችላሉ። እንዲሁም አሠልጣኞች በአናሳ ክፍሎች ላይ ስላለው የተዛባ አመለካከት፣ በተለይ በዘር ላይ ተመሥርቶና ፆታዊ አመለካከት ላይ ተመሥርቶ ስለሚነሣው የተዛባ አመለካከትን መቆጣጠር በሚያስችል መልኩ ሊሠለጥኑ ይገባል፤ ለዚህም ከናሙና ጥናቶችና በቅርብ ሊገኙ ከሚችሉ የጥሩ ልምድ ዘዴዎች ሊጠቀሙ ይገባል። ጥሩ አሠልጣኞች ሁልጊዜ ራሳቸው ሠራተኞች ናቸው ስለዚህም የአቻ ትምህርት በሁሉም ደረጃ የሚበረታታ ነው። ይህ ከሠራተኞች ተወካዮች ጋር በመመካከር ማደግ ያለበት ከሥራ ቦታ ዓመታዊ የሥልጠና እቅዶች አንዱ ሊሆን ይገባል።

## 7.1. ለሥራ አስኪያጆች፣ ተቆጣጣሪዎችና ለአስተዳደር ኃላፊዎች የሚሰጥ ሥልጠና

ለሠራተኞች ሁሉ በሚዘጋጁት የመረጃና ትምህርት ፕሮግራሞች ከመሳተፍ በተጨማሪ የቁጥጥርና የአሠራር ኃላፊዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ብቃት እንዲኖራቸው ሥልጠና ሊያገኙ ይገባል፦

- የሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲን አስመልክቶ ለሚነሡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠትና ለማስረዳት እንዲያስችላቸው፤
- ሠራተኞች በሥራ ቦታ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መስፋፋት ላይ ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት እንዲያስወግዱ ለመርዳት ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በቂ መረጃ ለማስያዝ፤
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች እስከ ተቻለ ድረስ መሥራት እንዲችሉ ተመጣጣኝ የመቻቻል አማራጮችን ማስረዳት፤
- በሥራ ቦታ ላይ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር በሚኖሩ ሠራተኞች ላይ የሚደርሰውን መድልዎ፣ ማግለል፣ ልምድና ጠባይ ለመለየትና ለመቆጣጠር፤
- ሊገኙ ስለሚችሉ የጤና አገልግሎቶችና ማኅበራዊ ጥቅሞች ምክር ለመስጠት እንዲያስችላቸው።

## 7.2. ለአቻ አስተማሪዎች (peer educators) የሚሰጥ ሥልጠና

አቻ አስተማሪዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ብቃት እንዲኖራቸው ሥልጠና ሊያገኙ ይገባል፡-

- በሙሉም ሆነ ወይም በከፊል ለሠራተኛው ኃይል የመረጃና የትምህርት ፕሮግራም መስጠት እንዲችሉ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መከላከል ይዘትና አሠራር በበቂ ሁኔታ እውቀት ያላቸው መሆን፤
- ሥልጠናን በሚያዳብሩበትና በሚሰጡበት ጊዜ ለዘር፣ ለፆታዊ አመለካከትና ለባህል ግምት ያላቸው መሆን፤
- እንደ ወሲባዊ መደፈርና በሥራ ቦታ ላሉት የአካል ጉዳተኞች ከተቀረጹት ተጨባጭ የሥራ ቦታ ፖሊሲዎች ጋር ማያያዝና ከእነርሱም መጠቀም፤
- የሥራ ባልደረቦቻቸው በሕይወታቸው ውስጥ ወደ በሽታ ከፍተኛ ጉዳት የሚያጋልጡ ምክንያቶችን እንዲለዩ ማስቻል፤
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ ሠራተኞች ሁኔታቸውንና መዘዞቹን እንዲቋቋሙ ምክር መስጠት እንዲችሉ ማድረግ።

## 7.3. ለሠራተኞች ተወካዮች የሚሰጥ ሥልጠና

የሠራተኞች ተወካዮች በሥራ ሰዓት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ብቃት እንዲኖራቸው ሥልጠና ሊያገኙ ይገባል፡-

- የሥራ ቦታ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲን አስመልክቶ ለሚነሡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠትና ለማስረዳት እንዲያስችላቸው፤
- በአሠልጣኝ የትምህርት ፕሮግራሞች ሌሎች ሠራተኞችን ለማሠልጠን እንዲያስችላቸው፤
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር በሚኖሩ ሠራተኞች ላይ መድልዎ የሚያደርግ የሥራ ቦታ የተለየ ጠባይ፤ ድርጊትና ልምድ ካለ እንዲህ ያለውን ድርጊት በአጥጋቢ ሁኔታ ለመዋጋት ለይቶ ማወቅ፤
- በሚጠየቅበት ጊዜ ተመጣጣኝ ድጋፍ እንዲያገኙ ከኤይድስ ጋር በተያያዘ መልኩ የታመሙ ሠራተኞችን መርዳትና መወከል፤
- ሠራተኞች በግል ሕይወታቸው ለአደጋ የሚያጋልጡ ምክንያቶችን እንዲለዩና እንዲቀነሱ ማማከር፤
- ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መስፋፋት ለሠራተኞች ለማሳወቅ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በመመሪያ ማወቅ፤
- የውክልና እንቅስቃሴዎቻቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ስለሚኖሩ ሠራተኞች የሚያገኙት ማንኛውም መረጃ በምሥጢር መጠበቁን ማረጋገጥ።

## 7.4. ለጤናና ለደህንነት ኃላፊዎች የሚሰጥ ሥልጠና

ለሠራተኞች ከታቀዱ የመረጃና የትምህርት ፕሮግራሞች ጋር የተዋወቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ የጤናና የደህንነት ኃላፊዎች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ነጥቦች ብቃት እንዲኖራቸው የተለየ ሥልጠና ሊያገኙ ይገባል፡-

- ለሠራተኞች የመረጃና የትምህርት ፕሮግራም እንዲሰጡ ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መከላከል ይዘትና አሠራሮች በበቂ ሁኔታ እውቀት ያላቸው መሆን፤
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞችን ተጎጂነት ለመቀነስ ሊለወጡ ወይም ሊሻሻሉ የሚችሉ የአሠራር ዘዴዎችና ሁኔታዎችን መለየትና የሥራ አካባቢን መዳሰስ መቻል፤
- አንድ አሠሪ አስተማማኝ የመጀመሪያ እርዳታ አሠራሮችን ጨምሮ ለሠራተኞች ጤናማና አስተማማኝ የሥራ ኣካባቢ ማዘጋጀቱን/ማዘጋጀቷን ማረጋጥ፤
- ማንኛውም ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የተያያዘ መረጃ እንደ ሌላው የሠራተኞች የህክምና መረጃዎች ሁሉ በጥብቅ ምሥጢርነት የሚጠበቅ መሆኑንና በዓለም ሥራ ድርጅት ስለ ሠራተኞች የግል መረጃ አጠባበቅ የአሠራር መመሪያ በተደነገገው መሠረት ብቻ ይፋ እንደሚወጣ ማረጋገጥ፤
- ሠራተኞች በግል ሕይወታቸው የጉዳት ጭብጦችን እንዲለዩና እንዲቀነሱ ማማከር፤
- ሠራተኞችን ለፍላጎቶቻቸው በአጥጋቢ ሁኔታ ምላሽ ሊሰጡ ወደሚችሉ በድርጅቱ ውስጥ ወይም ከዚያ ውጭ ወዳሉ የህክምና አገልግሎቶች ማስተላለፍ መቻል።

## 7.5. ለማምረቻ/ለሥራ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች የሚሰጥ ሥልጠና

አግባብነት ያለው ባለሥልጣን የማምረቻና የሥራ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች የቁጥጥር፣ የማጠናከርያና የምክር እንቅስቃሴዎቻቸውን እንደ ችሎታቸው ለማሟላት፣ በተለይ በድርጅቶች የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መከላከል በሚመለከት፣ ብቁ ዘዴዎች ያሉአቸው መሆኑን ማረጋጥ ይኖርባቸዋል። ይህንንም ለመቀዳጀት በሥራ ቦታ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ መከላከልና ጥበቃ ስልቶች ላይ ልዩ ሥልጠና መውሰድ ይኖርባቸዋል። ሥልጠናው የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፡-

- አግባብነት ስላላቸው ዓለም አቀፍ የሥራ ደረጃዎች፣ በተለይ የ1958ቱ የቅጥርና የሙያ መድልዎ ድንጋጌ (ቁ. 111)፤ እንዲሁም ብሔራዊ ሕጎችና ደንቦች መረጃ ፤
- ለሠራተኞችና ለአመራራቸው ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ግንዛቤ ስለ መስጠት፤
- በመደበኛ ሙያዊ ደህንነትና የጤና መግለጫዎች ውስጥ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ርዕሶችን መጨመር እንዴት እንደሚቻል፤
- ሠራተኞች ያሉ ጥቅሞችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ (ለምሳሌ የጥቅም ቅፆችን መሙላት) እና በሌሎች ሕጋዊ መብቶች እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መርዳት፤
- የኤች.አይ.ቪን ሁኔታ አስመልክቶ የሠራተኞችን መብት ስለ መጣስና ተግባራዊ አለመሆን እንዴት መለየት ስለሚቻል፤

- ከዚህ መመሪያ ጋር በሚስማማ መልኩ ለበሽታው ምርምርና ለሚያሳድረው ማኅበራዊ ተጽእኖ ጥናት በሥራ ቦታዎች ከቫይረሱ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ስለ መሰብሰብና መተንተን ችሎታዎች፡፡

## 7.6. ከሰው ደምና ከሌሎች የሰውነት ፈሳሶች ጋር ለሚነካኩ ሠራተኞች የሚሰጥ ሥልጠና

ሠራተኞች ሁሉ በሥራ ቦታ በሚፈጠሩ አደጋዎችና በመጀመሪያ እርዳታ እይታ ውስጥ በሽታን ስለ መቆጣጠር አሠራሮች ሥልጠና ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ፕሮግራሞቹ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ ሥልጠና የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡-

- የመጀመሪያ እርዳታ ስለ መስጠት፤
- ጠቅላላ ጥንቃቄዎች ለሰው ደምና ለሌሎች የሰውነት ፈሳሾች የመጋለጥን አደጋ ስለ መቀነስ (አባሪ 2 ውስጥ ተመልከት)፤
- የመከላከያ መሣሪያ ስለ መጠቀም፤
- ለሰው ደም ወይም ለሰውነት ፈሳሾች የመጋለጥ አጋጣሚ በሚኖርበት ወቅት ስለሚከተሉት ትክክለኛ አሠራሮች፤
- በሥራ ላይ  አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ ካሣ የመጠየቅ መብት፤

እንዲሁም የሚወሰዱት ጥንቃቄዎች ከግለሰቦች በተመገተ ወይም እርግጠኛ የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ ጋር የሚያያዙ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ፡፡

# 8. ምርመራ

በዚህ መመሪያ በተዘረዘረው መሠረት ካልሆነ በቀር የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ በሥራ ቦታ ሊደረግ አይገባም፡፡ ይህ አላስፈላጊና የሠራተኞችን ሰብአዊ መብትና ክብር አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡ የምርመራ ውጤቶች ይፋ ሊሆኑና በተዛባ መንገድ ግልጋሎት ላይ ሊውሉ ይችላሉ፤ የተባለውም የሠራተኞች ስምምነት ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ ነፃ ላይሆን ወይም በምርመራው ጭብጦችና ግኝቶች ላይ ያልተመሠረተ ሊሆን ይችላል፡፡ ከሥራ ቦታ ውጭ ቢሆንም እንኳ ምሥጢራዊ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ በሠራተኛው ስምምነት ላይ የተመሠረተና እንደ አመቺነቱ በሙያው ብቁ በሆነ ሠራተኛ፣ በጥብቅ የምሥጢራዊነት ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ መሆን አለበት፡፡

## 8.1. በምልመላና በቅጥር የሚደረግ ክልከላ

የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ በምልመላ ጊዜና በሥራ ሥምሪት ቀጣይነት ላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊጠየቅ አይገባም፡፡ ከቅጥር አስቀድሞ በመደበኛ መልኩ ሥራን ለመጀመር የሠራተኞችን ብቁነት ለማረጋገጥ፣ ወይም በሥራ ላይ ላሉ ሠራተኞች የሚደረግ ማንኛውም መደበኛ ምርመራ አስገዳጅ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራን መጨመር የለበትም፡፡

## 8.2. ለመድህን ዋስትና ዓላማዎች የሚደረግ ክልከላ

ሀ. ለብሔራዊ የማኅበራዊ ደህንነት አሠራር እቅዶች፣ ለጠቅላላ የዋስትና ፖሊሲዎች፣ ለሙያዊ ፕሮግራሞች፣ ለጤና ዋስትና ለመብቃት የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ እንደ መድህን ዋስትና ኩባንያዎች ቅድመ ሁኔታ ሊጠየቅ አይገባም።

ለ. የመድህን ዋስትና ኩባንያዎች ለአንድ የሥራ ቦታ ሽፋን ለመስጠት ከመስማማታቸው አስቀድሞ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ሊጠይቁ አይገባም። ወጪያቸውንና የማኅበራዊ ዋስትና መዋጮችና ክፍያዎች ግምት ባሉ የጠቅላላው ሕዝብ የበሽታ ቁጥጥር መረጃዎች ላይ ሊመሠርቱ ይችላሉ።

ሐ. አሠሪዎች ለመድህን ዋስትና ምክንያቶች ብለው ምንም ዓይነት የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ሊያመቻቹ አይገባም፤ አስቀድሞ በእጃቸው ያሉትም መረጃዎች በምሥጢርነት ሊቆዩ ይገባል።

## 8.3. የበሽታ ክትትል ጠቅላላ ጥናት

በሳይንሳዊ ምርምር ግብረ ገባዊ መርሆዎች፣ በሙያዊ ግብረ ገብነትና የግለሰብን መብቶችና ምሥጢራዊነት በመጠበቅ እስከ ሆነ ድረስ ያልታለመ፣ ከኤይድስ ያልተያያዘ ወይም ከጤና ጋር የተያያዘ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራ በሥራ ቦታ ሊደረግ ይችላል። እንዲህ ያለው ምርምር በሚደረግበት ቦታ ሠራተኞችና አሠሪዎች ይህ እንደሚሆን ሊነገራቸውና ሃሳባቸውን ሊጠየቁ ይገባል። የሚገኘው መረጃ በግለሰቦች ወይም በተወሰኑ ሰዎች ላይ መድልዎ ለማድረግ ማገልገል የለበትም። ከምርመራው ውጤቶች በመነሣት የአንድን ሰው የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታ ለማወቅ አሳማኝ እድል ካለ ምርመራው ያልታለመ ሊባል አይችልም።

## 8.4. በፈቃደኛነት መመርመር

ሠራተኞች በራሳቸው አነሣሽነት በሚካሄድ ፈቃደኛ የምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ምርመራ በሥራ ቦታ ሳይሆን በመደበኛ የአካባቢ የጤና አገልግሎት ጣቢያዎች ሊካሄድ ይገባል። የተሟላ የህክምና አገልግሎት ባለበት ስፍራ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ምርመራ በአንድ ሠራተኛ ጥያቄና በጽሁፍ በተገለጸ ስምነነት፣ ከተጠየቀም ከሠራተኞች ተወካዮች በሚሰጥ ምክር፣ ሊደረግ ይችላል። ምርመራው እንዳመቺነቱ በሠለጠነ ሠራተኛ የሚደረግ ሆኖ ለጉዳዩ በጥብቅ ምሥጢርነት መጠበቅና ይፋ ለማድረግ በሚያስፈልጉት መስፈርቶች ላይ በመስማማት መሆን አለበት። የፆታን ጥያቄ ትኩረት ውስጥ ያስገባ ከምርመራ በፊትና በኋላ የሚሰጥ የምክር አገልግሎት፣ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራዎችን ባሕርይና ዓላማ ግንዛቤ የሚያመቻች፣ የምርመራው ጥቅምና ጉዳት እንዲሁም በሠራተኛው ላይ ያለው ውጤት፣ የአንድ ምርመራ አሠራር መሠረታዊ አካል ሊሆን ይገባል።

## 8.5. በሥራ ምክንያት ከሚደርስ መጋለጥ በኋላ የሚደረጉ ምርመራዎችና ህክምና

ሀ. ለሰው ደም፣ ለሰውነት ፈሳሾችና ለህዋሳት መጋለጥ በሚኖርበት ጊዜ የሥራ ቦታ እንዲህ ያሉትን መጋለጦችና ሙያዊ የጉዳት አጋጣሚዎችን የሚቆጣጠርባቸው አሠራሮች በቦታው ሊኖሩት ይገባል፡፡

ለ. በሥራ ቦታ ለተበከለ መሣሪያ ከመጋለጥ በኋላ (ለሰው ድም፣ ለሰውነት ፈሳሾች ወይም ህዋሳት ሊሆን ይችላል)፣ ሠራተኛው አጋጣሚውን እንዲቋቋም፣ ስለ ህክምና ውጤቶች፣ ስለ ኤች.አይ.ቪ. ምርመራ አስፈላጊነትና ከመጋለጥ በኋላ ስለሚኖር የመከላከል ህክምና (Prophylaxis—ፕሮፊላክሲስ) ወዲያውኑ ምክር ሊሰጠውና ወደ ተገቢው የህክምና ተቋዋም ሊተላለፍ ይገባል፡፡ ጉዳትን ከመዳሰስ ድምዳሜ ቀጥሎ ለሠራተኞች ካሣ ለመጠየቅ ብቁነት ስለሚያስፈልጉ አሠራሮች ጨምሮ ስለ ሠራተኛው ሕጋዊ መብት ተጨማሪ መመሪያ መሰጠት አለበት፡፡

# 9. እንክብካቤና ድጋፍ

ለኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ምላሽ ለመስጠት አንድነት፣ ጥንቃቄና ድጋፍ የአንድ ሥራ ቦታ መመሪያ ወሳኝ አካሎች ናቸው፡፡ የኤች.አይ.ቪ. ሁኔታን ይፋ ለሚያወጡ ሠራተኞች ግልጽነትን፣ መቀበልንና ድጋፍን የሚያበረታቱ ዘዴዎች ሊፈጠሩ፣ መድልዎ እንዳይደረግባቸውና ዝቅ ተደርገው እንዳይታዩ የሚረጋገጥበት ዘዴ መፈጠር ይኖርበታል፡፡ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ወረርሽኝ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ለማለዘብ የሥራ ቦታዎች በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ለተጠቁና ለተጎዱ ሠራተኞች የምክር አገልግሎትና ሌሎች ማኅበራዊ ድጋፎች መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች በሥራ ቦታ በሚኖሩበት ጊዜ ተገቢ ህክምና መሰጠት አለበት፤ እነዚህ አገልግሎቶች ሊገኙ በማይችሉበት ቦታ ከዚያ ውጭ የት ሊገኙ እንደሚችሉ ለሠራተኞች ሊነገራቸው ይገባል፡፡ እንዲህ ያሉ መያያዦች ከሠራተኞች ባሻገር ለቤተሰቦቻቸው፣ በተለይ ለልጆቻቸው፣ እንዲዳረሱ ሽፋን ለመስጠት ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በመንግሥት፣ በአሠሪዎች፣ በሠራተኞችና በተወካዮቻቸው እንዲሁም አግባብነት ባላቸው አጋሮች መካከል የሚደረጉትን አጥጋቢ የአገልግሎት አሰጣጦችን ያረጋግጣል እንዲሁም ወጪዎችን ያድናል፡፡

## 9.1. ከሌሎች ከባድ ህመሞች ጋር ያለው አቻነት

ሀ. በሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ. በሽታና በሀኪም ክትትል ሥር ያለ ኤይድስ ከሌሎች ከባድ ህመሞች ባላነሰ ሁኔታ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

ለ. ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች ጥቅሞችን፣ የሠራተኞች ካሣና ተመጣጣኝ ማመቻቸትን በተመለከተ ሌላ ከባድ ህመም ካለባቸው ሠራተኞች ባላነሰ ሁኔታ ሊታዩ ይገባል፡፡

ሐ. ሠራተኞች ለተገቢ ሥራ ብቁ መሆናቸው በህክምና እስከ ተረጋገጠ ድረስ መደበኛ የሥራ ዋስትና፣ የዝውውርና የእድገት እድሎች ማግኘት ይኖርባቸዋል::

## 9.2. የምክር አገልግሎት

ሀ. አሠሪዎች ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች በምክር አገልግሎት ረገድ ከድርጅቱ ውጭ ያለውን ሙያና ድጋፍ እንዲጠቀሙና በድርጅቱ ውስጥ የሠለጠነና ምሥጢራዊ የምክር አገልግሎት የሚቀርብ ከሆነ የራሱን ሙያዊ የዋስትናና የጤና ክፍል፣ እንዲጠቀሙ ማበረታታት አለባቸው::

ለ. ይህም ውጤታማ እንዲሆን አሠሪዎች የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊያጤኑ ይገባል:-

- ባለሙያዎችን፤ ራስ አገዝ ቡድኖችና በአካባቢ ማኅበረሰብ ወይም በክልል ውስጥ ከቫይረሱ ጋር በተያያዘ መልኩ ምክር በመስጠትና በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ህክምና የሠለጠኑ አገልግሎቶችን መለየት፤
- ህክምና ነክ የሆኑና ያልሆኑ፣ በማኅበረሰብ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱና ከቫይረሱ ጋር ላሉ ሠራተኞች ጠቃሚ የሚሆኑ ድርጅቶችን መለየት፤
- አስቀድሞ የተደረገ ምርመራ ከሌለ ለመጀመሪያ ግምገማና ህክምና አንድ ሠራተኛ ዶክተሩን/ዶክተሯን ወይም የሠለጠነ የጤና አጠባበቅ መኰንን እንዲያይ/እንድታይ ሃሳብ መስጠት፤ ወይም ሠራተኛው የራሱ/የራሷ የሆነ ሀኪም ከሌላቸው የሠለጠነ የጤና አጠባበቅ መኰንን የሚገኝበትን ቦታ እንዲያውቁ መርዳት::

ሐ. አሠሪዎች ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ ሠራተኞች ከመሠረታዊ ብሔራዊ ግዴታዎች ጋር በሚስማማ መልኩ ለምክር አገልግሎትና ለህክምና ተመጣጣኝ የእረፍት ጊዜ መስጠት ይኖርባቸዋል::

መ. የምክር አገልግሎት ድጋፍ ያለ ምንም ወጪ የሚገኝና ለወንዶችና ለሴቶች የተለያዩ ፍላጎቶችና ሁኔታዎች የሚስማማ መሆን አለበት:: እንዲህ ያለውን ድጋፍ በመመሥረቱና በማቅረቡ ሂደት በመንግሥት፣ በሠራተኞችና በማኅበሮቻቸው፣ እንዲሁም አግባብነት ባላቸው አጋሮች መካከል ግንኙነት መፍጠር ይሆናል::

ሠ. የሠራተኞች ተወካዮች ከተጠየቁ ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች ሙያዊ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ መርዳት ይኖርባቸዋል::

ረ. የምክር አገልግሎቶች ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን መቋቋም እንዲችሉና ጥቅማቸውን በተመለከተ ስለ ሕጋዊ የማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች፣ ሙያዊ ፕሮግራሞችና ስለ ሌሎች የሕይወት ፕሮግራሞች ማሳወቅ ይኖርባቸዋል::

ሰ. በሥራ ምክንያት ለኤች.አይ.ቪ. መጋለጥ በሚኖርበት ጊዜ አሠሪዎች ለምክር አገልግሎት ዓላማ ከተመጣጣኝ ክፍያ ጋር ለሠራተኞች የእረፍት ጊዜ መስጠት ይኖርባቸዋል።

## 9.3. የሙያና ሌሎች የጤና አገልግሎቶች

ሀ. አንዳንድ አሠሪዎች ሠራተኞቻቸው የእድሜ ማራዘሚያ (Antiretroviral—አንቲሪትሮቫይራል) መድኃኒቶች እንዲያገኙ ለመርዳት በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ያሉ ይሆናሉ። በሥራ ቦታ የጤና አገልግሎቶች በሚኖሩበት ጊዜ ከመንግሥትና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አጋሮች ሁሉ ጋር በመተባበር ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ እንዲሁም ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞችን መርዳት በሚቻልባቸው ስፋት ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች መስጠት ይኖርባቸዋል።

ለ. እነዚህ አገልግሎቶች የእድሜ ማራዘሚያ (Antiretroviral—አንቲሪትሮቫይራል) መድኃኒቶች አቅርቦትን፣ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር በተያያዘ መልኩ የሚመጡ ሥቃዮችን ለማስታገስ የሚሰጥ ህክምናን፣ የአመጋገብ ምክርና ተጨማሪ እገዛዎችን፣ ድካም ማቅለልን፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላፉ በሽታዎችና ሳንባ ነቀርሳን ጨምሮ አመቺ ሁኔታን ተጠቅመው ለሚመጡ ተራ ህመሞች የሚሰጥ ህክምናን ያካትታሉ።

## 9.4. ከራስ አገዝና በማኅበረሰብ ላይ ከተመሠረቱ ቡድኖች ጋር የሚኖሩ ግንኙነቶች

ተገቢ በሚሆንበት ቦታ አሠሪዎች፣ የሠራተኞች ማኅበራትና መደበኛ የጤና ባለሙያዎች በድርጅቱ ውስጥ የራስ አገዝ ቡድኖችን መመሥረት፣ ወይም በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የተጠቁ ሠራተኞችን ወደ ራስ አገዝ ቡድኖች ማስተላለፍና ለአካባቢ ማኅበረሰብ ድርጅቶች ድጋፍ መስጠትና ማመቻቸት ይኖርባቸዋል።

## 9.5. ጥቅሞች

ሀ. መንግሥታት ከማኅበራዊ አጋሮች ጋር በመመካር በብሔራዊ ሕጎችና ድንጋጌዎች መሠረት ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች በሌሎች ከባድ ህመሞች ከተጠቁ ሠራተኞች ባላነሰ ሁኔታ ጥቅሞችን እንደሚያገኙ ማረጋገጥ አለባቸው። እንዲሁም በተለይ አዳጊና ተለዋዋጭ ለሆነው የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ባሕርይ የሚመለከቱ የአዲስ ጥቅሞች ቀጣይነትን መመርመር ይኖርባቸዋል።

ለ. አሠሪዎች፣ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ከመንግሥታት ጋር በመሆን የደመወዝ ድጎማ ዕቅዶችን ጨምሮ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ ሠራተኞች ፍላጎት የነባር ጥቅም አሠራሮችን መጽደቅ መከታተል አለባቸው።

## 9.6. የማኅበራዊ ዋስትና ሽፋን

ሀ. መንግሥታት፣ አሠሪዎችና የሠራተኞች ማኅበራት ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ከሙሉ ጠበቃ፣ ከማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችና ከሙያ ማሻሻያ ዕቅዶች እንዳይታገዱ ለማረጋጥ አስፈላጊውን እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው:: ይህ በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ አደጋ ላይ እንዳሉ ለሚታሰቡ የሙያዊና ማኅበራዊ ቡድኖች ለሆኑ ሠራተኞችና ቤተሰቦቻቸውን የሚመለከት መሆን አለበት::

ለ. እነዚህ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ከሌላ ከባድ ህመሞች ጋር ላሉ ሠራተኞች እንደሚደረገው ሁሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር ለሚኖሩ ሠራተኞችም ተመሳሳይ ጥቅሞች መስጠት አለባቸው::

## 9.7. ግለኝነትና ምሥጢራዊነት

ሀ. መንግሥታት፣ የግል መድህን ኩባንያዎችና አሠሪዎች ከምክር አገልግሎት ጋር የተያያዙ መረጃዎች፣ እንክብካቤዎች፣ ህክምናና የጥቅሞች አቀባበል፤ ልክ እንደ ሠራተኞች የህክምና መረጃዎች በምሥጢር መጠበቃቸውንና በ1985ቱ የዓለም ሥራ ድርጅት የመደበኛ ጤና አገልግሎቶች መሪ ሃሳብ (ቁ. 171) መሠረት ብቻ ሊታዩ እንደሚችሉ ማረጋገጥ አለባቸው::

ለ. ሦስተኛ ወገኖች፣ እንደ ባለ አደራዎችና የማኅበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች አስተዳዳሪዎች ያሉት፣ በዓለም ሥራ ድርጅት የሠራተኞችን የግል መረጃ አጠባበቅ መመሪያ መሠረት ከቫይረሱ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ሁሉ በምሥጢር መጠበቅ አለባቸው::

## 9.8. የሠራተኛና ቤተሰብ እርዳታ ፕሮግራሞች

ሀ. በወረርሽኙ ባሕርይ እይታ መሠረት የሠራተኛ እርዳታ ፕሮግራሞች እንደ ቤተሰብ አባልነታቸው የቤተሰብ አባሎችን ለማካተት፣ እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው አባላት ድጋፍ ለመስጠት እንዲችሉ ሆነው መመሥረት፣ ወይም በተገቢው መንገድ እንዲዳረሱ መሆን ይኖባቸዋል:: ይህ ከሠራተኞችና ከተወካዮቻቸው ጋር በመመካከር የሚደረግ ሲሆን በአቅምና በፍላጎት መሠረት ከመንግሥትና አግባነት ካላቸው አካሎች ጋር በመተባበር የሚፈጸም ይሆናል::

ለ. እንዲህ ያሉት ፕሮግራሞች ሴቶች ከኤይድስ ጋር በተያያዙ በሽታዎች ለታመሙት ከፍተኛውን የእንክብካቤ ድርሻ እንደሚወስዱ እውቅና ሊሰጡ ይገባል፤ እንዲሁም የነፍሰ ጡር ሴቶችን ልዩ ፍላጎት መገንዘብ አለባቸው:: በኤይድስ አንድ ወይም ሁለት ወላጆቻቸውን በማጣት ትምህርታቸውን ስለሚያቋርጡ፣ ከዚያም ለመሥራት የሚገደዱና በከፍተኛ ደረጃ ለወሲብ መጠቀሚያ ለሚሆኑ ሕፃናት ችግር ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል:: ፕሮግራሞቹ የውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ድርጅቶች

እንዲህ ያሉትን ፕሮግራሞች በጥቅሉ ሊደግፉ ወይም እንዲህ ያሉትን አገልግሎቶች ለገለልተኛ ድርጅት በኮንትራት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ሐ. የቤተሰብ እርዳታ ፕሮግራም የሚከተሉትን ሊጨምሩ ይችላሉ፡-

- ርኅራኄ የተሞላ የእረፍት ፈቃድ፤
- በመረጃና በትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ጥሪ ማድረግ፤
- ራስ አገዝ ቡድኖችን ጨምሮ ለድጋፍ ቡድኖች ማስተላለፍ፤
- ሥራው የትምህርት ሰዓትን የማይሻማ እስከ ሆነ ድረስ ለሠራተኛው ወይም ለቤተሰቡ አባላት አማራጭ የሥራ እድል እንዲያገኙ እገዛ ማድረግ፤
- በኤይድስ ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናትና ወጣቶች ችግር መፍቻ እንዲሆኑ የሚታቀዱ እንደ መደበኛ ትምህርት፣ ሙያዊ ሥልጠናና በሥራ ላይ ሥልጠና ያሉ የተለዩ እርምጃዎች፤
- የሠራተኞች ልጆች የሚማሩባቸውን ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ አግባብነት ካላቸው አካሎችና ማኅበረሰባዊ ድርጅቶች ጋር መተባበር፤
- ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የገንዘብ እርዳታ፤
- ከህመምናና ከጥገኞች ፍላጎቶች ጋር የተያያዙ የገንዘብ ጥያቄዎችን መቆጣጠር፤
- የሕግ መረጃ፣ ምክርና እገዛ፤
- በህመምና በሞት ጊዜ ሕጋዊ ሂደቶችን፣ ከህመም ጋር የተያያዙ የገንዘብ ጥያቄዎች፣ ኑዛዜና የውርስ እቅዶች የማዘጋጀት ግንዛቤን በመሚለከት እገዛ፤
- ቤተሰቦች ከማሕበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞችና ከሙያዊ ሥልጠና ፕሮግራሞች ጋር እንዲተዋወቁ መርዳት፤
- ለሠራተኛው የሚገባውን የቅድሚያ ክፍያ መስጠት፤
- ቤተሰቦች አግባብነት ወዳላቸው የሕግ ወይም የጤና ባለሥልጣኖች መምራት ወይም የጠቃሚ መሥሪያ ቤቶችን (ባለሥልጣኖችን) ዝርዝር መስጠት፡፡

# አባሪ 1

## ስለ ወረርሽኙና ውጤቶቹ መሠረታዊ ጭብጦች

### ስለ ኤች.አይ.ቪ. እና ኤይድስ ጭብጦች

ኤይድስን የሚያመጣው (Human Immunodeficiency Virus (HIV)—ህዩማን ኢምዩኖዲፊሽንሲ ቫይረስ—ኤች.አይ.ቪ) በሰውነት ፈሳሾች የሚተለላለፍ ነው፤ ከእነዚህም ደም፣ የወንዴ ዘር፤ የማኅፀን ፈሳሽና የጡት ወተት በተለይ የሚጠቀሱ ናቸው:: የመተላለፊያ መንገዶቹ አራት እንደ ሆኑ ተረጋግጧል፤ እነርሰም:- በበሽታው ከተያዘ/ከተያዘች ጓደኛ ጋር የሚደረግ ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት (በጣም የታወቀ)፣ በደምና በደም ውጤቶች፣ ለምሳሌ በተበከለ መርፌ መወጋትና በሰውነት አካል ወይም ህዋስ በመተካት (organ or tissue transplants)፤ በተበላሸ መርፌ ወይም ቆዳን በሚበሱ ለሎች መሣሪያዎች በመጠቀም፤ በበሽታው ከተያዘች እናት በእርግዝና ወይም ልጁ በሚወለድበት ጊዜ፤ እንዲሁም ጡት ማጥባት ናቸው::ኤች.አይ.ቪ በድንገተኛ የአካል መነካካት፣ በሳል፣ በማስነጠስ ወይም በመሳሳም፣ የመጸዳጃና የማጠቢያ ዕቃዎችን፣ የመመገቢያ ቁሳቁሶችን በጋራ በመጠቀም ወይም በኤች.አይ.ቪ የተያዘ ሰው የተነካ ምግብና መጠጥ በመውሰድ አይተላለፍም፤ እንዲሁም በትንኞች ወይም በሌሎች ነፍሳት ንክሻ አይስፋፋም::

ኤች.አይ.ቪ የአካልን የመከላከያ በማዳከም ሰውነት ህመምን እንዳይቋቋም ያደርጋል:: አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ በኋላ እስከ አሥር ዓመታት ሊቆይ ይችላል፤ ይኸውም ምንም እንኳ እርሱ በሽታውን ለሌሎች ሊያስተላልፍ የሚችል ቢሆንም፣ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ የሚበልጠውን ጊዜ የሚያሳልፈው ያለ አንዳች ምልክት ወይም ህመም ነው:: የኤይድስ የመጀመሪያ ምልክቶች ከፍተኛ ድካምን፣ ተቅማጥን፣ ትኩሳትን፣ እንደ መርሳት ያሉትን የሥነ አእምሮ ለውጦችን፣ የክብደት መቀነስን፣ የማያቋርጥ ሳልን፣ ተደጋጋሚ የሆነ የቆዳ መፈንዳትን፣ ችፍታና የአፍ መቁሰልን፤ እብጠትና የመጋጠሚያ ንፊፊቶችን ያካትታል:: እንደ ካንሰር፣ መንጋጋ ቆልፍ፣ የሳንባ ምችና የሳንባ ነቀርሳ ያሉ ምቹ ሁኔታውን ተጠቃሚ በሽታዎች የአካልን የመቋቋም ኃይል በማዳከም ሰውየውን በበለጠ ያጠቁታል:: ምን እንኳ የህመሙ ወቅት ከማስተላለፊያው ጊዜ ጋር የተለያየ ሊሆን ቢችልም በአብዛኛው ኤይድስ ገዳይ:: በአሁኑ ጊዜ ክትባቶች ለማግኘት ምርምር እየተካሄደ ነው፣ ሆኖም ገና ህልውና ያገኘ ነገር አይደለም:: የበሽታውን እድገት የሚቀንሱና ዕድሜን የሚያራዝሙ (Antiretroviral—አንቲሪትሮቫይራል) መድኃኒቶች ተፈጥረዋል፤ ባሁኑ ጊዜ ግን ዋጋቸው እጅግ ውድ ከመሆኑ የተነሣ ለብዙ በሽተኞች (ተሠቃዮች) አልተዳረሱም:: ሁኔታው ግን በፍጥነት እየተለወጠ ነው፤ ኤች.አይ.ቪ. በተወሰነ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ህልውና ሊኖረው የሚችል ደካማ ቫይረስ ነው:: ወደ ሰውነት ሊገባ የሚችለው በተፈጠሮ እርጥበታማ በሆኑ የአካል ክፍሎች ሲሆን ያልተበሳ ቆዳን ሊያልፍ አይችልም:: ስለዚህ መከላከሉ እንደ ኮንደም ወይም (አስፈላጊ ሲሆን) እንደ ጓንትና ጭንብል ያሉትን የመከላከያ በመጠቀም፣ ቆዳን የሚበሱ መሣሪያዎች ያልተበከሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ከቫይረሱ መራቅ ይቻላል:: ቫይረሱ ዕቃዎችን በመርዝ በማጠብ፣ በዕቃ ማጠቢያ መድኃኒቶችና በሙቅ ውሃ ሊሞት ይችላል (አባሪ 2 ተመልከት)::

## በሥነ ሕዝብና በሠራተኛ ኃይል ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ

*በ2000 ዓ.ም. መጨረሻ ከ36 ሚሊዮን በላይ ሕዝቦች ከቫይረሱ ጋር እየኖሩ ነበር፤ ከእነዚህ ሁለት ሦስተኛዎቹ ከሳሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች የሚገኙ ናቸው፡፡ ወደ 22 ሚልዮን የሚጠጉ ሰዎች በኤይድስ ሞተዋል፤ በ2000 ዓ.ም. 12 ወሮች ውስጥ በመላው ዓለም 3 ሚሊዮን ሕዝብ ሞቶአል፡፡*

*በዓለም ያሉ አካባቢዎች ሁሉ የተጠቁ ናቸው፤ ከሳሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ አገሮች 25 ሚልዮን፣ በእስያ ከ6 ሚልዮን በላይ፣ በላቲን አሜሪካና በካራብያን አገሮች ወደ 2 ሚልዮን ገደማ፣ በሰሜን አሜሪካ ከ1 ሚልዮን በታች፣ ግማሽ ሚልዮን በምዕራብ አውሮፖ፣ ወደ 175፡000 ገደማ በምሥራቅ አውሮፓና በመካከለኛው እስያ፣ ወደ ግማሽ ሚልዮን በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ተቆጥረዋል፡፡ ምንም እንኳ ከፍተኛው የስርጭት ዘዴው የተለያየ ቢሆንም የዓለም አካባቢዎች እያደገ የሚሄድ የበሽታ መጠን እያጋጠማቸው ነው፡፡*

*በአፍሪካ ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር በኤይድስ የመሞት ውጤት ግልጽ ነው፡፡ ከ2010 ዓ.ም. በፊት በ29 አገሮች በ2 በመቶ በሚስፋፋ ፍጥነት ጠቅላላው የሕዝብ ብዛት ኤይድስ በሌለበት ጊዜ ከነበረው በ50 ሚልዮን ያነሰ ይሆናል፡፡ እንዲሁም በብዙ አገሮች ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በወጣትነት ዕድሜ በበሽታው በመያዛቸው የፆታና የዕድሜ ውጤቶች አሉ፤ በአፍሪካ በበሽታው ለመጀመሪያ ከሚያዙት ከግማሽ በላይ ሴቶች ናቸው፡፡ በሁሉም ቦታ ክፉኛ የተጠቃው የዕድሜ ክልል ለቤተሰብ፣ ለኅብረተሰብና ለኤኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋጽኦ በሁኔታው የሚጠፋበት ከ15 እና 49 ዓመት የዕድሜ ክልል ያለው ነው፡፡ የዓለም ሥራ ድርጅት በመላው ዓለም ከ20 ሚልዮን በላይ ሠራኞች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ይገምታል፡፡ ከ2020 ዓ.ም. በፊት በሽታው በከፍተኛ ደረጃ በተስፋፋባቸው አገሮች የሠራተኛ ኃይል መጠን ኤይድስ ከመኖሩ በፊት ከነበረው ይልቅ በ10 እና 30 በመቶ ያነሰ ይሆናል፡፡ ከ14 ሚልዮን በላይ ሕፃናት በኤይድስ ከወላጆቻቸው አንዱን አጥተዋል፤ ብዙዎቹም ከትምህርት ቤት እንዲባረሩና ወደ ሥራ እንዲሰማሩ አስገድዶቸዋል፤ ይህም በራሱ የሕፃናት ሠራተኛነት ችግር እንዲያመረቅዝ አድርጎአል፡፡*

*ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በበሽታው በተያዙ ግለሰቦች፣ በቤተሰቦቻውና በጠቅላላው ማኅበረሰብ ታላቅ ተጽእኖ አሳድሮአል፡፡ የሚያስከትለው ችግር የተጠቂዎቹ ጥገኛ በሆኑ ሽማግሌዎችና ወጣቶች ላይ ውጤቱ ከባድ ነው፡፡ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ ያሳደረው ተጽእኖ በድርጅትና በይበልጥም በብሔራዊ ኤኮኖሚ ደረጃ ይንጸባረቃል፡፡ ወረርሽኙ በሥራው ዓለም ራሱን በተለያ መንገድ ይገልጻል፤ ይኸውም በምርት መቋረጥ፣ በቅጥር ጊዜ በሚደረግ መድልዎ፣ የፆታ እኩነትን ጥያቄ ወደ መጥፎ ድረጃ በማድረስና የሕፃናትን ሠራተኛነት ሁኔታ በማሳደግ ነው፡፡ ሌሎቹ ክስተቶች የተመናመነ የሰው ሀብት፣ በጤናና በማኅበራዊ ዋስትና አሠራር ላይ ግፊት ማሳደርና የሙያዊ ደህንነትና የጤንነት ለአደጋ መጋለጥ ናቸው፡፡*

## ለተጎጂነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎች

### አጠቃላይ ጭብጦች

ኤይድስ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች በተጣሱበት፣ እንዲሁም የዜግነትና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች በተዛቡበት ቦታ ያድጋል። በኤኮኖሚያዊ ጎኑ ድህነት እንደ መሃይምነትና መገፋት (marginalization) ያሉት ዋነኛ የድህነት ጭብጦች ድሆችን በበለጠ ተጎጂ ያደርጋቸዋል፤ በሴቶች ላይ ባልተጠበቀ የወሲብ ንግድ ላይ በመሰማራት እንዲኖሩና ቤተሰቦቻቸውን እንዲደግፉ ግፊት ያደርግባቸዋል። ዝቅተኛ አመጋገብ፣ በቂ ያልሆነ መኖሪያና የንጽሕና ጉድለት በኤች.አይ.ቪ. የተያዘን ሰው ከኤይድስ ጋር በተያያዙ ህመሞች በበለጠ ተጎጂ ያደርጉታል። በማኅበራዊና ባህላዊ ጎኑ በግልና በሥራ ግንኙነቶች እኩል አለመሆን በአደገኛ ሁኔታዎች ወደ አላስፈላጊ ወሲብ ይመራሉ። እንዲሁም አመለካከቶችና ጠባይ አደጋውን እንደሚጨምሩ ጭብጦች ተደርገው ሊታወቁ ይገባል። ኤች.አይ.ቪ. ሱስ አስያዥ ዕፆችን በደም ሥር በተበከለ መርፌ በመወጋት ይተላለፋል። የዕፅና የአልኮል ሱስ የአንድ ግለሰብን ጤናማ የወሲብ ልምድና የመርፌ አጠቃቀም ችሎታ ሊያዳክመው ይችላል። ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በሚኖሩ ሰዎች ላይ የሚደርሰው መዋረድ ስለ በሽታው ያለመናገር ዝንባሌን ያሰፍናል፤ ይህም ለመስፋፋቱ የሚረዳ ይሆናል። ባህላዊ ግፊቶችና አለመቀበል ለበሽታው መጠን በአካባቢና በብሔራዊ ደረጃ ሽፋን ይሰጡታል፤ ይህም ለማኅበረሰቦችና ለግለሰቦች ውጤታማ ምላሽ ለማቀድ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

በሕዝባዊና ፖለቲካዊ ጎኑ፣ የግጭት ሁኔታዎች፣ የሕግና ሥርዓት ውድቀት፣ ብልሹ የሕግ መዋቅርና የማጠናከሪያ አሠራር ዘዴዎች፣ የመደራጀትና የኅብረት ስምምነት መብቶች መገፈፍ እድገትን በአጠቃላይ ይገታሉ፣ እንዲሁም በተለይ መሠረታዊ የጤና ማሳደግ እርምጃዎችን ያዳክማሉ። በብዙ አገሮች አስቀድሞ በዕዳና በኤኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ሳቢያ የተዳከሙ በዝቅተኛ ሁኔታ የተዋቀሩ የጤና አጠባበቅ አሠራሮች የተፈለገውን ጥንቃቄና መከላከል ሊያቀርቡ አልቻሉም።

በአጠቃላይ መድልዎና የሰብአዊ መብቶች መከበር ጉድለት ሠራተኞች በበሽታው ይበልጥ ተጎጂ እንዲሆኑና ፈቃደኛ ምርመራን፣ የምክር አገልግሎትን፣ ህክምና ወይም ድጋፍን ለመፈለግ አስቸጋሪ ስለሚሆንባቸው ኤይድስን ለመቋቋም እንዳይችሉ አድርጓቸዋል። እንዲሁም በድጋፍና በመከላከል ዘመቻዎች ሊተሳፉ አይችሉም።

### በአንዳንድ ሠራተኞች ዘንድ የበሽታውን አደጋ የሚያሳድጉ ጭብጦች

ምንም እንኳ ዋናው ጥያቄ ሙያን ሳይሆን ጠባይን የሚመለከት ቢሆንም አንዳንድ የሥራ ዓይነቶች ከሌሎቹ ይልቅ ለበሽታው አደጋ የሚያጋልጡ ናቸው። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ለዚህ አመልካች ዝርዝር ነው፦

- እንቅስቃሴ ያለበት ሥራ፣ በተለይ በሥራ ምክንያት በመደበኛ ሁኔታ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር ምክንያት ከትዳር ጓደኛ ወይም ፍቅረኛ ርቀው እንዲቆዩ የሚያደርግ፤

- የተወሰነ ማኅበራዊ ግንኙነትና የተወሰነ የጤና አገልግሎቶች ባሉባቸው በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ተለይቶ መሥራት፤

- በአንድ ፆታ ተለይቶ በወንዶች መካከል የመኖርና የመሥራት ሁኔታ፤

- ሠራተኛው በበሽታው ላይ የመካላከል ቁጥጥር ሊያደርግ የማይችልባቸው ሁኔታዎች፤

- ሴቶች በጣም አነስተኛ የሆኑበትና ወንዶች የበዙበት የሥራ ዓይነት፤

- ከሰው ደምና ከደም ውጤቶችና ከሰውነት ፈሳሾች ጋር እንደ መነካካት፣ በመርፌ መቁሰልና ለተበከለ ደም እንደ መጋለጥ ያሉ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች ባልተጠበቁባቸው እና/ወይም በቂ መሣሪያ በሌለበት ሁኔታ የሚፈጠሩ ሙያዊ አደጋዎች።

እንደ ሥራ ሊቆጠሩ የማይችሉ ሁኔታዎች በዚህ ዝርዝር ሊካተቱ ይችላሉ፣ ማለትም የሥራ እድል ያላገኙ ሠራተኞች፣ አንድ ዓይነት ገቢ ለማግኘት ተስፋ በማድረግ በከተማ ማእከሎች እንደ መሰባሰብ ያሉት ለኤች.አይ.ቪ. በቀላሉ ለሚዳርጉ ግፊቶች የተጋለጡ ናቸው፤ ተፈናቃይ ሰዎችና የስደተኞች መጠለያ ኗሪዎች በዚህ ውስጥ ይካተታሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ባዶነትና የመገለል ስሜት ወደ ወሲብ ሊለወጥ ወይም ወደዚያ ለመግባት ሊያስገድድ ይችላል፤ በተለይ ብዙ ብቸኛ እናቶች እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።

## መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ ያሉ ልዩ ፍላጎቶች[1]

መደበኛ ባልሆነው የኤኮኖሚ ዘርፍ ያሉ ሠራተኞች በኤይድስ ውጤቶች ለመሠቃየት በተለይ የተጋለጡ ናቸው:: ምክንያቱም በመጀመሪያ በመደበኛ ቅጥር ያሉ ሠራተኞች የሚያገኙትን የጤና አገልግሎቶችና የማኅበራዊ ጥበቃ ጥቅሞች ለማግኘት አለመቻላቸው፣ ሁለተኛ እንቅስቃሴአቸው ገንዘብ በማግኘት ላይ የተመሠረተው አልፎ አልፎ በመሆኑ፤ እንዲሁም ሦስተኛ የሥራቸው ጠባይ ጊዜያዊና ተጎጂ መሆን በንግዳቸው ወይም በምርታቸው ላይ አንዳች ጉድለት ሊያስከትል እንደሚችል ያመለክታል:: መደበኛ ሳልሆኑ ድርጅቶች አንድ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ሠራተኞችን በማጣት ወደ ድርጅቱ መፍረስ የሚያመሩ ዋነኛ ተጽኖዎች ይኖሩታል:: ባለቤቱ ኤች.አይ.ቪ. ቢይዘው ይታመምና ይሞታል፤ በውጤቱም የድርጅቱ ተቀማጭ ለህክምና፣ ለእንክብካቤና ለቀብር ማስፈጸሚያ ስለሚውል ወደፊት በሌላ ሥራ ላይ መዋሉ ይቀራል፤ ኪሳራን ያመጣል፤ እንዲሁም ጥገኛ ሠራተኞችና የቤተሰብ አባሎችንና የቅርብ ዘመዶቻቸውን በሞት እንዲጠቁ ያደርጋቸዋል:: በገጠሩ መደበኛ ባልሆነው ዘርፍ የጥንቃቄው ሸክም የሠራተኛው ከእርሻ እንቅስቃሴዎች መዘናጋት ሲፈጠር በኤይድስ ሠራተኛውን ኃይል በማጣት ምክንያት ዝቅተኛ የምግብ ምርትና የረጅም ጊዜ የምግብ ክምችት ማነስን ያስከትላል:: በአጠቃላይ ከዚህ በታች የተገለጸው ሂደት ሲከሰት ወደታች የሚያሽቆለቆለው የኤኮኖሚ መስመር መደበኛ ባልሆኑት ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ስሜትን የሚፈጥር ነው፤ ይኸውም:- ሸማቾች ሲሞቱ ወይም ለጤና አያያዝና ለጥንቃቄ ከሚያወጡት ዋጋ የተነሣ አነስተኛ ገቢ ሲኖራቸው ነው::

## የፆታ ገፅታ

ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ በተጎጂነትና በተጽእኖ አኳያ ወንዶችና ሴቶችን በተለያየ መንገድ ያጠቃል:: በሴቶች ሁኔታ የአካል እኩል አለመሆን በሽታውን የመከላከሉን እርምጃ አስቸጋሪ ስለሚያደርግባቸውና የኤይድስን ተጽእኖ በእነርሱ ላይ ስለሚያበረታባቸው ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን ለበሽታው ተጎጂ የሚያደርጉ ሥነ ሕይወታዊ (ባዮሎጂያዊ) ጭብጦች አሉ::

[1] በ1991 ዓ.ም. በዓለም *ሥራ* ድርጅት ጉባኤ ላይ በዋና ዳይሬክተሩ በቀረበው *ሪፖርት* ላይ እንደ ተገለጠው:- «*መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ*» ሸቀጦችን በአነስተኛ ደረጃ የሚያመርቱና የሚያከፋፍሉ አገልግሎት የሚሰጡ፣ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች በከተሞች አካባቢ ያሉና በአብዛኛው ራሳቸውን የቻሉ፣ በራሳቸው የሚሠሩ አምራቾች፣ ከእነዚህም አንዳንዶቹ የቤተሰቦቻቸውን አባላት እና/ወይም የተቀጠሩ ጥቂት ሠራተኞችን ወይም ረዳቶችን የሚያሠሩ:: እነዚህ በጣም አነስተኛ በሆነ ተቀማጭ የሚንቀሳቀሱ፣ ወይም ምንም የሌላቸው፤ ዝቅተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂና ሙያ የሚጠቀሙ፣ ስለዚህም በዝቅተኛ የአምራችነት ደረጃ የሚንቀሳቀሱ፣ በአጠቃላይ ዝቅተኛና መደበኛ ያልሆነ ክፍያ የሚሰጡና በውስጣቸው ለሚሠሩት በከፍተኛ ደረጃ ያልተረጋጋ የቅጥር ሁኔታ ያለባቸው ናቸው:: በሕጋዊ የመረጃ ጥናት ያልተመዘገቡና ያልተጻፉ በመሆናቸው መደበኛ አይደሉም፤ ከተደራጁ ገበያዎች፣ ከብድር ተቅዋሞች፣ ከመደበኛ ትምህርትና ማሠልጠኛ ተቅዋሞች፣ ወይም ከብዙ ሕዝባዊ አገልግሎቶችና መዝናኛዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት አነስተኛ ነው ወይም ምንም የላቸውም፤ መንግሥት የሚታቁ፣ የሚደገፉ ወይም ቁጥጥር የሚረግባቸው አይደሉም፤ ሁልጊዜ ከሕግ አሠራር ውጭ ባሉ ሁኔታዎች ለመንቀሳቀስ የሚገደዱ ናቸው፤ የተመዘገቡና አንዳንድ የሕግ ገጽታዎችን የሚያከብሩ ቢሆኑም እንኳ በአብዛኛው ከማኅበራዊ ጥበቃ፣ ከሠራተኛ ድንጋጌና ከሥራ ቦታ ከለላዊ እርምጃዎች ውጭ ናቸው:: መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ አምራቾችና ሠራተኞች (ምን እንኳ በተለያዩ እንቅስቃሶዎች የተሰማሩ መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ማኅበራት ቢኖሩም) በአጠቃላይ ያልታወቁ፣ በአብዛኛውም ከሠራተኛ ማኅበራትና ከአሠሪዎች ድርጅቶች የእርምጃ ዓላማ ውጭ ናቸው:: (የዓለም *ሥራ* ድርጅት ጉባኤ፤ *መደበኛ ያልሆነው ዘርፍ አጣብቂኝ*፡ 78ኛ ጉባኤ 1991፣ *ሪፖርት* 1፣ ገጽ 4፣ በእንግሊዝኛ የተጻፈ)::

- ብዙ ሴቶች በጋብቻቸው ወይም በግንኙነቶቻው ለኤኮኖሚያዊና ወሲባዊ የበታችነት ይዳረጋሉ፤ ስዚህም ጥንቃቄ ያለበትን ወሲብ ሊደራደሩ ወይም ያልተጠበቀ ወሲብን ላለመቀበል አይችሉም::

- በሥራ ቦታ የሥልጣን አለመመጣጠን ሴቶችን ለወሲባዊ ጥቃት ያጋልጣቸዋል::

- ድህነት ለኤይድስ ተጎጂነት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው፣ ሴቶችም ከዓለም ድሆች ከፍኛውን ደረጃ ይይዛሉ፤ በድህነት ቀውስ ከትምህርት ቤት ተባርረው ለግዳጅ ሥራና ለወሲብ አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ የሚጋለጡት ወጣት ልጃገረዶች ናቸው::

- ሴቶች የመከላከሉ መልእክት እንዳይደርሳቸው በመሃይምነት ተገትተዋል፤ ይኸውም በመላው ዓለም ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን ያጠቃ፣ በአንዳንድ አገሮች በእጥፍ ብዛት ያለው ሁኔታ ነው::

- በአገሮች ውስጥ በሚከሰቱ ፍልሰቶች ሴቶች ከፍተኛውን ድርሻ ከመያዛቸው የተነሣ ከልጆቻቸው ጋር የስደተኞችን 75 በመቶ ይወክላሉ፤ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ከአማካይ በላይ ከኤች.አይ.ቪ. በሽታ አደጋ ጋር የተዛመዱ ናቸው:: ግጭት ባለበት ሁኔታ በተዋጊ አንጃዎች የሚፈጸም አስገድዶ የመድፈር ወንጀል አለ::

- በኤች.አይ.ቪ. የተጠቁ የቤተሰብና የማኅበረሰብ አባላትን የመንከባከቡ ሸክም አዘውትሮ በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ይወድቃል፤ ስለዚህም የሥራ ጫና ይጨምርባቸዋል፣ የገቢ ምንጭ ለመፍጠርና ለመማር ያላቸው እድል ያነሰ ይሆናል::

- ከኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ጋር የሚኖሩ ሴቶች ወላጆቻቸውን በሞት ስላጡ ወይም በኤች.አይ.ቪ. በመያዛቸው ስለ ተገለሉ ገንዘብ የማግኘት ዋስትናና ኤኮኖሚያዊ እድል እንደ ተነፈጉ የፆታ መድልዎ ተከራካሪዎች፣ የውርስ፣ የጥበቃና የድጋፍ ሕጎች ያመለክታሉ፤ ይህም በፋንታው በወሲብ ንግድ ሥራ እንዲኖሩ ያስገድዳቸዋል:: በተለይ ወጣት ልጃገረዶች ለወሲብ ንግድ መጠቀሚያነት የተጋለጡ ናቸው::

- ጥናቶች በተለይ በገጠር አካባቢዎች ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሴቶች ከኤይድስ ጋር በተያያዘ ለጎጂ አመለካከትና ለመገለል በበለጠ ተጎጂ መሆናቸውን ያሳያሉ፣ ከዚህ የተነሣ የተተዉና የተገፉ ይሆናሉ፤ ይህም ሕይወታቸውን በወሲብ ሥራ እንዲመሩ ጫና ይጨምርባቸዋል::

- ሴቶች የሚያካሄዱት ሥራ፣ የሚከፈልበት ወይም ያልታወቀ ቢሆንም፣ በኤይድስ በቀላሉ ይመሰቃቀላል:: ለምሳሌ በማኅበራዊ ዋስትና ወይም በመደበኛ የጤና አጠባበቅ ባልተሸፈኑ ሥራዎች ሴቶች መደበኛ ያልሆነውን ዘርፍ ይቆጣጠራሉ::

- ከወንዶች ያነሰ ጥቂት ሴቶች በማኅበራዊ ዋስትና ወይም ከሙያ ጋር በተያያዙ የጤና አጠባበቅ ጥቅሞች የተሸፈኑ ናቸው፡፡

- ወንዶች በተለመደ የተብአታይ (masculine) ባሕርይ መከላከያ ለሌለውና በፍላጎት ላይ ላልተመሠረተ የወሲብ ግንኙነት ሰለባዎች ናቸው፡፡

- በተጎጂ ሠራተኞች ምድብ ወንዶች በቁጥር በልጠው ቀርበዋል፤ ይህም በሥራቸው በወንዶች መካከል ለሚደረግ ላልተጠበቀ ወሲብ በሚያጋልጡ ሁኔታዎች ውስጥ ራሳቸውን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡

- በወንዶችና በሴቶች መካከል ካለው የሥልጣን ግንኙነት አኳያ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን የመከላከልና የመታገል አሠራሮች በማጽደቁና የሃላፊነት አቋሞችን በማበረታታት ረገድ ወንዶች ከፍተኛ ሚና መጫወት ይኖባቸዋል፡፡

# አባሪ 2

## *በሥራ ቦታ የሚደረግ የበሽታ ቁጥጥር*

### ሀ. ጠቅላላ የደምና የሰውነት ፈሳሽ ጥንቃቄዎች

«*ጠቅላላ ጥንቃቄዎች*» ወይም «*መደበኛ ጥንቃቄዎች*» በስፋት ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ወረርሽኝና የሆስፒታል ሠራተኞችን ከደም-ወለድ በሽታዎች ለመከላከል ለመጀመሪያ ጊዜ የታቀዱት በዩናይትድ ስቴትስ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማእሎች በ1985 ዓ.ም. ነው፡፡ አዲሱ አቀራረብ ሰዎች ሁሉ እንዳለባቸው የሚታሰበውን በሽታ ግምት ውስጥ ሳያስገባ የደምና የሰውነት ፈሳሾች ጠቅላላ ጥንቃቄዎችን ሥራ ላይ በማዋሉ ላይ አጽንኦት አስቀምጧል፡፡

ጠቅላላ ጥንቃቄዎች ሁልጊዜ በደም ውስጥ የሚፈጠሩ የፓቶጂንስ ህዋሳትን ለመቀነስና ህመምተኞችን ለመንባከብ የሚጠቅሙ ቀላልና መደበኛ የበሽታ መቆጣጠሪያ ልምዶች ናቸው፡፡ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታሉ፡-

- ሹል ወይም ስለታም ነገሮችን በጥንቃቄ መያዝና መጣል (መርፌ ወይም ሌሎች ስለታም ነገሮች)፤

- ከማንኛውም ተግባር አስቀድሞ እጅን መታጠብ፤

- ከደምና ከሰውነት ፈሳሾች ጋር መነካካት በሚኖርበት ጊዜ የእጅ ጓንት፣ ጋውንና ጭምብል የመሳሰሉትን በማጥለቅ ጠባቂ ማገጃዎችን መጠቀም፤

- በደምና በሰውነት ፈሳሾች የተበከለ ቆሻሻን በመመሪያ መጣል፤

- የተበከሉ መሣሪያዎችንና ሌሎች ዕቃዎችን በተገቢው ማጽዳት፤ እና

- የውስጥ ልብሶች ተገቢ አያያዝ፡፡

## ለ. ምርጥ መመሪያዎች በመከላከያ ቁጥጥር ላይ ጠቅላላ ጥንቃቄዎች

Bednarsh, H.S.: "Infction Control: Universal Precautions reconsidered", in *American Dental Hygenists' Association: Access* (Chicago, 1995) Vol. 11, No. 1.

Centers for Disease Control and Prevention (CDC)/National Center for HIV, STD and TB Prevention/Division of HIV/AIDS prevention: *Preventing occupational HIV transmission to health care workers* (updated June, 1999).

South African Law Commission: *Aspect of the law relating to AIDS* (Projecct No. 85): Universal workplace infection control measures (Universal Precautions) (1997).

WHO: *WHO guidelines on AIDS and first aid in the workplace,* WHO AIDS series 7 (Geneva, 1990).

WHO/UNAIDS/ICN (International Council of Nurses): *HIV and the workplace and Universal Precautions,* Fact sheets on HIV/AIDS for nurses and midwives (Geneva, 2000).

# አባሪ 3

## በሥራ ቦታ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲ ስለ ማቀድና ተግባራዊ የማድረግ መከታተያ ዝርዝር (ማመሳከሪያ)

አሠሪዎች፣ ሠራተኞችና ተወካዮቻቸው ለፍላጎቶቻቸው ምላሽ የሚሰጥና ሚዛናዊ የሆነ የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ፖሊሲ በመቅረጹ ሂደት ግልጽና የቀና በሆነ ሥርዓት ሊተባበሩ ይገባል፡፡ ፖሊሲው በከፍተኛ ደረጃ በተወሰደ የቁርጠኛነት አቋም በመታገዝ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ለጠቅላላው ማኅበረሰብ አርአያ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መመሪያ ክፍል 6—9 በተብራራው መሠረት የዚህ ፖሊሲ ዋነኛ ነገሮች ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤይድስና እንዴት እንደሚተላለፍ መረጃን፣ የግል ግንዛቤንና ችሎታን የማሳደግ ስልቶችና ትምህርታዊ እርምጃዎችን፤ የጠባይ ለውጥን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ተግባራዊ የመከላከል እርምጃዎችን፤ ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩት እነርሱ ይሁኑ ወይም ቤተሰቦቻቸው ለተጠቁ ሠራተኞች ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግን፤ እንዲሁም በሥራ ቦታ ለሚደረግ ማንኛ ውም ዓይነት መጥፎ ስም መስጠትና መድልዎን ያካትታል፡፡

የሚከተሉት እርምጃዎች ፖሊሲና ፕሮግራም ለመቅረጽ እንደ መመሪያ ያገለግላሉ፡-

- ❑ የበላይ አመራር፣ የተቆጣጣሪዎች፣ የሠራተኞች፣ የሠራተኛ ማኅበራት፣ የሰው ኃይል ሃብት ክፍል፣ የሥልጠና ክፍል፣ የኢንዱትሪ ግንኙነቶች ክፍል፣ የመደበኛ ጤና ክፍል፣ የጤናና የደህንነት ኮሚቴ፤ እንዲሁም ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ተወካዮች ያሉበት የኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ ኮሚቴ ይቋቋማል፤
- ❑ ኮሚቴው የራሱን የሥራ መመሪያ የመወሰንና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንና ሃላፊነትን ይወስናል፤
- ❑ ብሔራዊ ሕጎች ለድርጅቶች ያላቸውን ተጽእኖ ይገመግማል፤
- ❑ ኮሚቴው በምሥጢር የመነሻ ጥናት በማካሄድ ኤች.አይ.ቪ. በሥራ ቦታ ያሳደረውን ተጽእኖና በኤች.አይ.ቪ/ኤይድስ የተያዙና የተጠቁ ሠራተኞችን ፍላጎት ይመረምራል፤
- ❑ ኮሚቴው በሥራ ቦታና በአካባቢ ማኅበረሰብ ምን ዓይነት የጤናና የመረጃ አገልግሎቶች እንዳሉ ያረጋግጣል፤
- ❑ ኮሚቴው በረቂቅነት ለአስተያየት ተሰራጭቶ የሚከለስና የሚጸድቅ ረቂቅ ፖሊሲ ያወጣል፤

- ኮሚቴው አስፈላጊ ሲሆን ከድርጅቱ ውጭ መዋጮ በመፈለግ ባጀት ያወጣል፤ እንዲሁም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ነባር የገቢ ምንጮች ይለያል፤

- ኮሚቴው ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ከጊዜ ሠንጠረዥና ከሃላፊነት መስመሮች ጋር የሥራ ዕቅድ ያወጣል፤

- ፖሊሲና የሥራ ዕቅድ እንደ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ዳብዳቤዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ልዩ ስብሰባዎች፣ ለአዲስ ሠራተኞች በሚሰጡ ኮርሶችና የሥልጠና ስብሰባዎች በሰፊው ይሰራጫሉ፤

- ኮሚቴው የፖሊሲውን ተጽእኖ ይቆጣጠራል፤

- በቫይረሱ የውስጥ ቁጥጥርና የውጭ መረጃ እንዲሁም በሥራ ቦታ ያስከተለውን ሁኔታ አስመልክቶ ኮሚቴው ፖሊሲውን በየጊዜው ይገመግማል።

ከላይ የተገለጹት እርምጃዎች በቀጣይነትና በማያቋርጥ ሁኔታ በታቀደ፣ በሚተገበርና ቁጥጥር በሚደረግበት አጠቃላይ የድርጅት ፖሊሲ ውስጥ መካተት ይኖባቸዋል።